# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ 82ኛ ዓመት ቁጥር 046 ጥቅምት 16 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


# መከላከያ ሳይንስና ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሃገራችንን ወደ ብልጽግና ማሻገር ይጠበቅበታል ሲሉ የቀድሞ የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት አሳሰቡ

- የሕግ ማስከበር ዘመቻን የሚዳስሰው “የእሳት ቀለበት” የተሰኘ መጽሐፍ ተመረቀ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የኢፌዲሪ መከላከያ ሠራዊት በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ግንባር ቀደም ሚናውን በመጫወት አገራችንን ወደሚጠበቀው የብልጽግና ማማ ማስቀመጥ እንደሚገባው የቀድሞ የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሙላቱ ተሾመ አሳሰቡ፡፡ የሕግ ማስከበር ዘመቻን የሚዳስስ “የእሳት ቀለበት” የተሰኘ በመከላከያ ጠቅላይ መምሪያ የተዘጋጀ መጽሐፍ ተመረቀ፡፡

የቀድሞው የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሙላቱ ተሾመ ትናንት የመከላከያ ቀን በተከበረበትና መጽሐፉ በተመረቀበት ወቅት ተገኝተው ባደረጉት ንግግር፤ የኢትዮጵያ ታሪክ እከሌ እንደጻፈው ተብሎ የሚጠቀሰው የባህር ማዶ ሰው ነው፡፡ ታሪኩ ሲጻፍ በታሪኩ ባለቤት ሳይሆን በሌላ ሰው ነው፡፡ አሁን ላይ ከዚያ በመሻገር የራሳችን ታሪክ ራሳችን መጻፋችን ሊበረታታ የሚገባው ተግባር ነው፡፡

ትውልድ አንዱ ከአንዱ በቅብብሎሽ ተቀብሎ ወደፊት ሀገርን እንዲያራምድ ታሪክ ወሳኝነት አለው፡፡ የሚጻፈው ታሪክ ትውልድን የሚቀርጽ መሆን አለበት፡፡ ይህ የሚሆነው ከአለፉት አባቶቻችን መልካሙን እየወሰደ የማይወሰዱትን ነገሮች ደግሞ ወደ ኋላ እየተወ በአገር ግንባታው የበለጠ አስተዋጽኦ ሲያደርግ መሆኑን ዶክተር ሙላቱ ገልጸዋል፡፡

መከላከያ ሳይንስና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ-ገባቦ ገብሬ

# በመተከሉ “ስለኢትዮጵያ” መድረክ፡-

- ለሀገር አንድነትና ሉዓላዊነት ሁሉም አርበኛ ሊሆን እንደሚገባ፤
- እየተከናወኑ ያሉ የልማት ተግባራት ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና እንደሚያሻግሩ፤
- የዓባይ ተፋሰስን ማልማት የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ መሆኑ ተወስቷል!

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመተከል ዞን ግልገል በለስ ከተማ ያዘጋጀው 12ኛው "ስለ ኢትዮጵያ" የፓናል መድረክ "ልማት በተግባር ስለኢትዮጵያ" በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት ተካሂዷል፡፡

መድረኩን የመሩት የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አሻድሊ ሀሰን ኢትዮጵያ ችግሮችን የምታልፍ ሀገር ስለመሆኗ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ማሳያ ነው ብለዋል። ርዕሰ መስተዳድሩ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ለማስተጓጎል የታሠበው ሴራ ከሽፎ በድል ተሻግረናል ነው ያሉት ።

የዓባይ ግድብ ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጅነር ክፍሌ ሆሮ ባቀረቡት መነሻ ጽሑፍ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሀብትም የታደለች አገር ናት፤ ነገር ግን ይህንን

በመተከሉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ:-ሃዲሽ አብርሃ






# “መንግሥት እያደረገ ያለው ሰብዓዊ ድጋፍ እና የመሠረተ ልማት ጥገና የትግራይ ሕዝብን ከከፋ ስቃይ ይታደጋል”

- አረጋዊ በርሄ(ዶ/ር)
የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ለትግራይ ሕዝብ እያደረገ ያለው ሰብዓዊ ድጋፍ እና የወደሙ መሠረተ ልማቶችን መልሶ የመጠገን እንቅስቃሴ ለሕዝቡ ስነልቦናዊ መታደስ

መንግሥት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ-ፀሐይ ንጉሤ

# ተማሪዎች በጥረታቸው ብቻ ውጤት ማግኘት ይኖርባቸዋል ብለን ያስቀመጥነውን ግብ አሳክተናል

- ትምህርት ሚኒስቴር

ገጽ 4




ትምህርት ቤቱ ለሠራዊቱ ልጆች ነፃ የትምህርት ዕድል ሰጠ

ገጽ 3

# “የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ጠላትን እያሳፈረና ሕዝብን ነጻ የማውጣት ተልዕኮውን በድል እየተወጣ ይገኛል”

- ብርጋዴር ጀኔራል ኃይሉ ጎንፋ
የቀድሞ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከፍተኛ መኮንን

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በጠንካራ ስነ ልቦና የተደራጀ ከውስጥ እና ከውጭ የተነሱ የኢትዮጵያ ጠላቶችን በከፍተኛ መስዋዕትነት እያሳፈረና ሕዝብን ነጻ የማውጣት ተልዕኮውን በድል እየተወጣ የሚገኝ ሠራዊት መሆኑን ብርጋዴር ጄኔራል ኃይሉ ጎንፋ ገለጹ፡፡

የቀድሞ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከፍተኛ መኮንን እና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ብርጋዴር ጄኔራል ኃይሉ ጎንፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ሠራዊት በአስተሳሰብ ደረጃ ሕዝባዊና እና ሀገራዊ ሠራዊት ሆኖ የተደራጀ፣ ጠላቶችን ሊመክት የሚችል ቁመና የተላበሰ እና ኢትዮጵያውያንን ያኮራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

እየተካሄደ ባለው ጦርነትም ሠራዊቱ ራሱ እየሞተ ሰው እንዲኖር እያደረገ ይገኛል ያሉት ብርጋዴር ጄኔራል ኃይሉ፤ ከአነስተኛ ደመወዙ ቀንሶ ጤና ተቋም፣ ትምህርት ቤት በየአካባቢው ሲገነባ ኖሯል፤ በከሃዲዎች በጀርባ የተመታውን ሳያስታውስ ሕዝብ ነጻ የማውጣት ሥራን በድል እየተወጣ የሚገኝ በመሆኑ የሚያኮራ የኢትዮጵያ ዓርማ ነው ብለዋል፡፡

በውስጥና በውጭ ከፍተኛ ጫና እና ተጽዕኖ እንደነበር ያስታወሱት ብርጋዴር ጄኔራል ኃይሉ፤ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ኢትዮጵያን እንደ አገር ማስቀጠል ችሏል ነው ያሉት፡፡ የሠራዊቱ የግዳጅ አፈጻጸሙ፤ ምኞቱ፣ ፍላጎቱ፣ ግቡም ሀገርን የማስቀጠል ዓላማ ያነገበ በመሆኑ ሕዝባዊነቱን ማስመስከር መቻሉንም አመልክተዋል፡፡

የሚሊቴሪ ዶክትሪን የሚፈቅድለትን፣ ኢትዮጵያ እና ዓለም በደረሱበት ደረጃ ማዕከል ባደረገ መልኩ ራሱን በአስተሳሰብ፣ በትጥቅ፣ በብቃት ያሻሻለ እና ዘመናዊ ሠራዊት የሆነ መሆኑንም ነው ብርጋዴር ጄኔራል ኃይሉ የጠቆሙት፡፡

ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሲመኙ የነበሩ ጠላቶችን ሊመክት የሚችል ቁመና የተላበሰ፣ ጠንካራ ስነ ልቦና ያለው ሆኖ የተደራጀ በመሆኑ ከውስጥና ከውጭ የተነሱ ጠላቶችን ከፍተኛ መስዋዕት በመክፈል ኢትዮጵያን እንደ አገር ማስቀጠል የቻለ ነው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በዓለም ከሚታወቅበት ጉዳይ አንዱ በሥነ ምግባሩ ነው፡፡ በሩቅ ምስራቅ በተሰጠው ግዳጅ በአግባቡ የተወጣ፣ በቅርቡም በጎረቤት ሀገራት በሰላም ማስከበር ግዳጁ የተባበሩት መንግሥታት የሰላም አስከባሪ ማዕቀፍ ውስጥ መልካም ስም ማትረፍ የቻለ ነው ብለዋል፡፡

ሠራዊቱ በአፍሪካ ውስጥም፤ በሩዋንዳ፣ ብሩንዲ፣ ኮንጎ፣ ላይቤሪያ፣ ሶማሊያ፣ ሱዳንና በደቡብ ሱዳን በሰላም ማስከበር ግዳጁ ራሱን መስዋዕት በማድረግ በሀገራቱ



ብርጋዴር ጄኔራል ኃይሉ ጎንፋ

መረጋጋት እንዲፈጠር በማድረግ የሚደነቅ ሥራ የሠራ ነው፡፡

ሀገራዊ እሴቱን ወደ ቀጠናዊ ጉዳዮች ከፍ በማድረግ የተደራጀ በመሆኑ በአካባቢው ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ ረገድ ትልቅ ስም ያተረፈ በአፍሪካ ስመ ጥር ሠራዊት ተገንብቷል ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሠራዊት ታሪኩ ከድሮ እየተወራረሰ የመጣ ነው፡፡ በመሐል የመንግሥታት ለውጦች ቢኖሩና ቢያዳክሙትም ታሪኩና ጀግንነቱ ከኢትዮጵያዊነት ጋር ተያይዞ የመጣ መሆኑንም ነው የገለጹት፡፡

በፊት እንመራበት የነበረው ዲሲፕሊንና በሕዝብ ፊትም ሰንደቅ ዓላማ ይዘን ቃል የገባነው ለሀገራችን፣ ለሕዝባችን እና ለሕገ መንግሥቱ ተጠሪ ሆነን እንሠራለን ብለን ነው፡፡ በቃላችን መሠረት ብዙ ጀግኖች አፍርተናል፣ ብዙ ጀግኖችም ለኢትዮጵያ ተሰውተዋል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

ብዙዎች ደግሞ ከቀደሙት ተምረው በሠራዊት ውስጥ ነበሩ፡፡ ለውጡ ሲመጣም የመከላከያ ሠራዊት አልፈረሰም፡፡ ሠራዊቱን ለማፍረስ ብዙ ሥራዎች ተሠርተዋል፤ ነገር ግን ሀገራዊ፣ ማኅበራዊ እሴት እና ቃል የገባበት ሀገራዊ ግዴታ በመኖሩ አልፈረሰም፡፡ በፊት ከነበረው የበለጠ ተጠናክሮ እየተደራጀ ይገኛል ነው ብርጋዴር ጄኔራል ኃይሉ ያሉት፡፡




# የመከላከያ ሠራዊት ተልዕኮ አሸባሪው ሕወሓት ሰብዓዊ ጋሻ ያደረጋቸውን ዜጎች ነጻ ማውጣት ነው

-የወቅታዊ ሁኔታ መረጃ ማጣሪያ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- “የሀገር መከላከያ ሠራዊት ዋንኛ ተልዕኮ የሽብር ቡድኑን ወታደራዊ አቅም ማዳከምና ቡድኑ ሰብዓዊ ጋሻ ያደረጋቸውን ንጹሓን ዜጎች ነጻ ማውጣት ነው” ሲል የወቅታዊ ሁኔታ መረጃ ማጣሪያ ገጽ አስታወቀ።

የሽብር ቡድኑ “ንጹሓን ዜጎች ጉዳት ደርሶባቸዋል” በሚል በርካታ ያቀናበራቸው ሐሰተኛ ተንቀሳቃሽ ምስሎች በማስረጃነት መገኘታቸውን አመልክቷል።

የወቅታዊ ሁኔታ መረጃ ማጣሪያ ገጽ ትናንት ባወጣው መግለጫ፤ አሸባሪው ሕወሓት በጦር ሜዳ የገጠመውን ከፍተኛ ሽንፈት ለመሸፋፈን በቁጥጥሩ ስር ያሉ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም “ንጹሓን ዜጎች እየሞቱ ነው በሚል ዲፕሎማሲያዊ ጫና እንዲፈጠር ሙከራ እያደረገ ነው” ሲል አስታውቋል።

የሽብር ቡድኑ “የንጹሓን ዜጎች ሞት” ሐሰተኛ ትርክት ዓላማ "ለአደጋ ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በተለይም የሴቶችና ሕጻናት ጉዳትና ሞት ዓለም አቀፍ ቁጣና ውግዘት ያመጣልኛል” የሚል እንደሆነ አመልክቷል።

የሀገር መከላከያ ሠራዊት ዋንኛ ተልዕኮ የሽብር ቡድኑን ወታደራዊ አቅም ማዳከምና ቡድኑ ሰብዓዊ ጋሻ ያደረጋቸውን ንጹሐን ዜጎች ነጻ ማውጣት እንደሆነ ገልጿል።

ሁሉም ተዋጊ አሐዶች በግጭት ቀጠናዎች የንጹሓን ዜጎችን ጥበቃን አስመልክቶ በቂ ስልጠና መውሰዳቸውንና በተለያዩ ቀደምት የግዳጅ አፈጻጸማቸው ስኬታማ መሆኑን ማስመስከራቸውን አመልክቷል።

“አሸባሪው ሕወሓት ንጹሓን ዜጎችን አደጋ ላይ በመጣል ሐሰተኛ ተጎጂዎችን በመፈብረክ” በርካታ ያቀናበራቸው ሐሰተኛ ተንቀሳቃሽ ምስሎች በማስረጃነት መገኘታቸውን ገልጿል።

በሌላ በኩል “የአየር ድብድባ ተፈጽሟል በሚል ከሰሞኑ ሲሰራጩ የነበሩ ምስሎች አግኝቻለሁ” ያለው የማጣሪያ ገጹ ምስሎቹ ሐሰተኛና በተባሉት ቦታዎች ምንም አይነት እርምጃ አለመወሰዱን አስታውቋል ሲል ኢዜአ ዘግቧል።

# ተመድ ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚመጥን ማሻሻያ እንዲያደርግ ኢትዮጵያ ጥሪ አቀረበች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚመጥን የተሻሻለ፣ ብቁ እና ሊተገበር የሚችል ማሻሻያዎችን እንዲያደርግ ኢትዮጵያ ጥሪ አቀረበች፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከትናንት ወዲያ የተከበረውን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቀን አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ፤ የተመድ መሥራች አባል የሆነችው ኢትዮጵያ በፈረንጆቹ አቆጣጠር 1945 በሥራ ላይ ለዋለው የድርጅቱ ቻርተር ጽንሰ ሐሳቦች ተፈጻሚነት በቁርጠኝነት እየሠራች መሆኗን ገልጿል።

ለዓለም ሰላምና የጋራ ደኅንነት ካላት ጉልህ አስተዋጽኦ አኳያም ኢትዮጵያ ከፈረንጆቹ 1950ዎቹ መጀመሪያ አንስቶ ለተመድ የሰላም ማስከበር ተልዕኮዎች ከፍተኛ ሚና እየተጫወተች መሆኗን አመልክቷል።

ኢትዮጵያ በተመድ ቻርተር እና መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳቦቹ ያሉ የባለብዙ ወገን መርሆዎችን እያከበረች በምትገኝበት ወቅት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚመጥን የተሻሻለ፣ ብቁ እና ሊተገበር የሚችል ማሻሻያዎችን እንዲያደርግም ጥሪ ታቀርባለች ሲል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ገልጿል።

የዓለም አቀፍ የባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲ ለሰዎች አንገብጋቢ ፈተናዎች የተሻለ ምላሽ ለመስጠት ሁሉን አቀፍ፣ አሳታፊ፣ ፍትሐዊና ወካይ ሊሆን እንደሚገባውም በመግለጫው ተገልጿል።

የባለብዙ መስክ አሳታፊነት ከተመድ ቻርተር ምሰሶዎች ጋር የተጣጣመ መሆን እንዳለበትም መገለጹን ኤፍቢሲ ዘግቧል፡፡



# ትምህርት ቤቱ ለሠራዊቱ ልጆች ነፃ የትምህርት ዕድል ሰጠ

**ዳግማዊት ግርማ**




አዲስ አበባ፡- ፓሺን አካዳሚ ለጀግናው የሀገር መከላከያ ሠራዊት አባላት ልጆች ያለውን ክብር ለማሳየት ለሠራዊቱ ልጆች ነፃ የትምህርት ዕድል መስጠቱን አስታወቀ፡፡ ትምህርት ቤቱ "ስለተሰዋልን ደም እና አጥንት ስለተከፈለልን ሕይወት ዘላለማዊ ክብር ለኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት" በሚል መሪ ቃል በትላንትናው ዕለት የመከላከያ ሠራዊት ቀንን አክብሯል፡፡

የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር አቶ ታደለ ሣህሌ እንደገለፁት ትምህርት ቤቱ ከቤታቸው ወጥተው ቁርና ሀሩር ሳይበግራቸው አገልግሎት እየሰጡ ለሚገኙ የጀግናው መከላከያ ሠራዊት አባላት ልጆች የነፃ ትምህርት እድል ሰጥቷል።

ፓሺን አካዳሚ ደሙን አፍስሶ ሀገር ለሚያስቀጥለው ሠራዊት ያለውን ክብር እያሳየ ነው ያሉት ርዕሰ መምህሩ፤ መከላከያ ሠራዊት ያለውን ጥልቅ አክብሮትም ለሁለት ዙር ደሙን በመለገስና የቁሳቁስና ገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ጭምር ነው የገለፀው ብለዋል።

እንደ ርዕሰ መምህሩ ንግግር ፤ ትምህርት ቤቱ ለጀግናው መከላከያ ሠራዊት ያለውን ጥልቅ የፍቅር ስሜትና አክብሮት ለመግለፅ ነው በዓሉን የነገ ሀገር ተረካቢዎች ከሆኑት ተማሪዎቹ ጋር ቀኑን ያከበረው።

ርዕሰ መምህሩ የነገ ሀገር ተረካቢ ትውልድ እንዲፈራ የሀገር ሰላም ወሳኝ እና ቁልፍ ጉዳይ በመሆኑ መከላከያ ሠራዊት እየከፈለ ላለው የሕይወት ተጋድሎ ክብር መስጠት ያስፈልጋልም ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ባለብዙ ታሪክ ሀገራችንን ለማፈራረስና በአንድነት ተከባብሮ የኖረውን ሕዝብ ለመነጣጠል በውጭና በሀገር ውስጥ ኢትዮጵያ ጠል ኃይሎች ትንኮሳ መፈፀማቸውን ርዕሰ መምህሩ አውስተዋል፡፡

ርዕሰ መምህሩ ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች በትንኮሳቸው ውድ ዋጋ ቢያስከፍሉም ሠራዊቱ ከፍተኛ ድል እያስመዘገበ የሕዝቡን ሰላም የሚያስጠብቅበት ዋዜማ ላይ መገኘታችንን ጠቅሰው ለመከላከያ ሠራዊት ያላቸውን ክብርና ምስጋና አቅርበዋል፡፡

የቀድሞ የኢትዮጵያ ሠራዊት የድጋፍና ልማት ማኅበር ፕሬዚዳንት ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ አማረ በበኩላቸው እኔ ሞቼ እናንተ ኑሩ ለሚለው ሠራዊት ክብር መስጠት አኩሪ ተግባር መሆኑን ገልጸዋል።

ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ እንደተናገሩት፤ ፓሽን አካዳሚ የቀጣይ ትውልድ አካላት ከሆኑት ተማሪዎች ጋር ቀኑን ማክበሩና ልጆቹን በሀገር ፍቅር እንዲሞሉ አድርጎ ማሳደጉ የሚያስመሰግነው በሌሎችም ትምህርት ቤቶች ትምህርት ሊወሰድበት የሚገባ ተግባር ነው፡፡

የኢፌዴሪ ሀገር መከላከያ ሠራዊት ቀን ጥቅምት 15 ቀን 1900 ሠራዊቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የጦር ሚኒስቴር ተብሎ የተመሠረተበትን ቀን ምክንያት በማድረግ የሚከበር ሲሆን የመከላከያ ሠራዊት ቀን "ሕዝባችን የጥንካሬያችን ምንጭ " በሚል መሪ ሀሳብ በዛሬው ቀን እንደሚከበር መገለፁ ይታወሳል ።

በዓሉ የአካዳሚው ሠራተኞች፣ተማሪዎች ፣ የመከላከያ ሠራዊት አባላት እና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት በተለያዩ ሁነቶች ነው ተከብሮ ውሏል፡፡



## መዲናዋን ተመራጭ የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ ነው

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- አዲስ አበባን ተመራጭ የቱሪዝም መዳረሻ ከተማ ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ባህል፣ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ ፡፡ በዓለም ለ43ኛ በሀገራችን ለ35ኛ ጊዜ የዓለም የቱሪዝም ቀን በአዲስ አበባ ደረጃ ተከብሯል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ አቶ ዣንጥራር አባይ ለ35ኛ ጊዜ የዓለም የቱሪዝም ቀን "አዲስ እሳቤ ለቱሪዝም" በሚል መሪ ቃል በአዲስ አበባ ትናንት ሲከበር እንደገለጹት፤ አዲስ አበባን ተመራጭ የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ ነው፡፡ ከእነዚህ ሥራዎች መካከልም የከተማዋን የቱሪዝም መስህቦችን ማስተዋወቅ፤ አዳዲስ መዳረሻዎች ማልማትና አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል ይገኙበታል፡፡

የሀገር ውስጥና የውጭ አገር ጎብኝዎችን ፍሰት በመጨመር ቱሪዝም ኢኮኖሚውን በመደገፍና የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድ ትልቅ ሚና አለው ያሉት ምክትል ከንቲባው፤ አዲስ አበባን በኮንፍረንስ ቱሪዝም ፣ በስፖርት ፓርክ ፣በሙዚየም፣ በሃይማኖታዊና ባህላዊ በዓላት የቱሪስት መናኻሪያ እንድትሆን ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ከተማ አስተዳደሩ በሚቀጥሉት ዓመታት ቱሪዝምን ከተለያዩ የልማት ሥራዎች ጋር በማስተሳሰር ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጥቅሞችን ለማረጋገጥ በአሠራርና በቴክኖሎጂ አደራጅቶ ድጋፍ የማድረጉን ተግባር አጠናክሮ እንደሚቀጥልም ተናግረዋል ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ባህል፣ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሣው በበኩላቸው የቱሪዝም ዘርፍ በዓለም ላይ ላለፉት 40 ዓመታት ከፍተኛ እምርታ ያሣየ ነው፡፡ በሀገራችን ዘርፉን የሚፈትኑ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ክስተቶች ቢያጋጥሙም መንግሥት ለዘርፉ በሰጠው ትኩረት መሻሻሎችን አሳይቷል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መንግሥት ለዘርፉ ልዩ ትኩረት በመስጠት ለቱሪዝም መስህብ የሚሆኑ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በቢሊዮን የሚቆጠር ሀብት በማፍሰስ እንዲለሙ አድርጓል ያሉት ኃላፊዋ፤ አዲስ አበባ ከነዋሪዎቿ ባሻገር የሌሎች አገሮችን ቀልብ በመሳብ የኩራት ምንጭ በመሆን ላይ የምትገኝ ከተማ ናት ብለዋል፡፡

አካታች ማኅበራዊ ትስስርን በማጎልበት፤ የተፈጥሮ፣ የታሪክና የባህል ቅርሶችን በመጠበቅና የቱሪዝም መዳረሻዎችን በማልማት አሁንም የጎብኝዎችን ፍሰት መጨመር እንደሚገባ ጠቁመው፤ በዚህም የሥራ ዕድልን በመፍጠርና የዜጎች ኑሮ በመሻሻል ቱሪዝም ዘርፉ እንዲያገግም ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ጥሪ አቅርበዋል ፡፡

35ኛው ሀገር አቀፍ የቱሪዝም ቀን 'አዲስ እሳቤ ለቱሪዝም' በሚል መሪ ቃል እየተከበረ ነው፡፡ በአዲስ አበባም ለ3 ቀናት የሚቆይ ዐውደ ርዕይ በመስቀል አደባባይ ተከፍቷል። ዐውደ ርዕዩ የአዲስ አበባ ምክትል ከንቲባ አቶ ጃንጥራር አባይ እና ሌሎች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት ለጎብኚዎች ክፍት ሆኗል።

## በ2015 መጨረሻ 169 የፌደራል ተቋማት የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሥርዓትን ተግባራዊ ያደርጋሉ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በያዝነው ዓመት መጨረሻ 169 የፌደራል ተቋማት የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሥርዓትን ተግባራዊ እንደሚያደርጉ የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን አስታወቀ።

በትናንትናው ዕለት የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ 1 ሺህ ከሚሆኑ የንግዱ ማኅበረሰብ ጋር የምክክር መድረክ ተካሂዷል።

የምክክር መድረኩን ንግግር በማድረግ የከፈቱት የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሐጂ ኢብሳ እንደገለጹት፣ በዚህ ዓመት መጨረሻ 169 የፌደራል ተቋማት ሥርዓቱን ይጠቀማሉ። በአሁኑ ጊዜ 73 የፌዴራል ተቋማት ተግባራዊ አድርገውታል። እንዲሁም ሰባት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቢሮዎች ሲስተሙን ተጠቅመው ሥራዎችን እየሠሩ ነው ብለዋል።



**አቶ ሐጂ ኢብሳ**

የኦሮሚያ ክልል በቅርቡ ወደ ሲስተሙ ለመግባት ዝግጅቱን አጠናቋል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ሌሎች ክልሎችም ከሁለት እስከ አምስት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ሲስተሙን ተጠቅመው ሥራቸውን ይሠራሉ ብለዋል። በመቀጠል ወደ ዞንና ወረዳ በማውረድ አገሪቷ ሙሉ ለሙሉ ከማንዋል የግዥ ወደ ኤሌክትሮኒክስ ግዥ ትሸጋገራለች፤ ይህም በተለይ የመንግሥትን ወጭ ከአምስት እስከ ሃያ አምስት በመቶ አላግባብ ለግዥ የሚወጣውን ወጭ ይቀንሳል ሲሉም ተናግረዋል።

ለግዥ ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ ይወጣ የነበረው የአበል፣ የጉዞ፣ የጊዜ ብክነት፣ የመኪና ነዳጅና መሰል ወጭዎች ሙሉ ለሙሉ እንዲቀነሱ ያደርጋልም ብለዋል።

የግዥ ሥርዓቱ በዘር፣ በሀይማኖትና በተለያዩ አድሏዊ አሠራር የተተበተበ በመሆኑ ያለው ችግር ከፍተኛ ነው ያሉት አቶ ሐጂ፤ በሲስተም ሲሆን ተወዳዳሪውን ማወቅ አይቻልም፤ አድሏዊ ሥራ መሥራት አይቻልም። በቀጣይ ለአቅራቢዎች በቂ ስልጠና ስለተዘጋጀ ሊፈጠር የሚችል ምንም አይነት ችግር አይኖርም ሲሉም ጠቁመዋል።

ሥርዓቱ የኢትዮጵያ የግዥ አሠራር ከባህላዊ ወደ ዘመናዊ የግዥ ሥርዓት የሚያሸጋግር ነው ያሉት አቶ ሐጂ፤ እንዲሁም የግለሰቦችን፣ የአቅራቢዎችንና የመንግሥትን ወጭን ይቀንሳል፤ ጨረታ በወረቀት ማስነገር ስለሚያስቀር ለወረቀት ይወጣ የነበረውን ወጭ ሙሉ ለሙሉ ያስቀራል። እንዲሁም ከጅምሩ ጀምሮ ኢንሳ ክትትል እያደረገ በመሆኑ ምንም ዓይነት የሲስተም መስተጓጎል አይኖርም ብለዋል።

ሳምኮን ኢንጂነሪንግን ወክለው በውይይት መድረኩ የተገኙት አቶ ሳሙኤል ሳሕለማሪያም በበኩላቸው፤ ሥርዓቱ ለሀገራችን የሚያስፈልግና ከጊዜው ጋር የሚሄድ ነው። የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሥርዓትን መጀመሩ የግዥ ሥርዓቱን በማስተካከል ይዘረፍ የነበረውን ሀብት ያድናል ሲሉም ተናግረዋል።

"ከዚህ በፊት ጨረታዎች በጋዜጣ ይታተሙና፤ የጨረታ ዶክመንት ለመውሰድ ስንሄድ ዶክመንቱ አልቋል፣ የግዥው ኃላፊ የለምና ሌሎች ምክንያቶች እየተፈጠሩ ከመጉላላት ባሻገር ፍትሐዊ ባልሆነ መንገድ አንዱ እንዲያሸንፍ ያደርጋሉ። አሁን ይህን ብልሹ አሠራር እንዲቀር በማድረግ ፍትሐዊ ተወዳዳሪነትን ይፈጥራል" ብለዋል።

ሲስተሙ አንድ ተጫራች ከቦታ ቦታ ሳይንቀሳቀስ በተቀላጠፈ መንገድ እንዲወዳደር ያደርገዋል ያሉት አቶ ሳሙኤል፤ ባለበት ሁኖ የመጫረቻ ዶክመንቶችን ማግኘትና መወዳደር ያስችለዋል። የንግዱ ማኅበረሰብም በፍጥነት ሊጠቀመው ይገባል። ብዙ ሀገሮች ይህን መሰል የግዥ ሥርዓት መጠቀም ከጀመሩ ቆይተዋል፤ በዚህም ከሙስና የጸዳ አሠራርን አስፍነዋል። ሲስተሙ መረጃ ሰብረው ከሚገቡ ኃከሮች የተጠበቀ መሆን አለበት ሲሉ አሳስበዋል።

# ተማሪዎች በጥረታቸው ብቻ ውጤት ማግኘት ይኖርባቸዋል ብለን ያስቀመጥነውን ግብ አሳክተናል

## - ትምህርት ሚኒስቴር

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- የ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና ተማሪዎች በጥረታቸው ብቻ ውጤት ማግኘት ይኖርባቸዋል ብለን ያስቀመጥነውን ግብ ያሳካንበት ነው ሲል ትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተናን አስመልክተው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ትምህርትን ለፖለቲካ ትግል መሣሪያ ለመጠቀም በተደረገ ያልተገባ እንቅስቃሴ በፈተና አስተዳደር ላይ ብዙ ጉዳት ሲደርስ መቆየቱን ተናግረዋል፡፡

በተለይም ባለፉት ሦስት ዓመታት የፈተና ዝግጅት፣ አሰጣጥ እና እርማትን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ለማድረግ የተጀመሩ እንቅስቃሴዎች የነበሩ ቢሆንም ለዚሁ ሥራ የሚያስፈልጉት የቴክኖሎጂ ግብዓቶች ባለመሟላታቸው ተግባራዊ ሳይደረግ መቆየቱን አውስተው፣ የፈተና አስተዳደር ችግር እንደ ሀገር በሕዝብና በመንግሥት ላይ ያደረሰውን ስብራት ለማከምና የትምህርት ሥራን አካዳሚያዊ ካልሆኑ ጣልቃ ገብነቶች ለመከላከል በርካታ ሥራዎች ሲሠሩ መቆየታቸውን አብራርተዋል፡፡

በተለይም ተማሪዎች የልፋታቸውን ውጤት ብቻ የሚያገኙበት ሥርዓት መገንባት አስፈላጊ መሆኑን በመንግሥት በተሰጠ ቁርጥ አመራር ሀገራችን በሰሜኑ ክፍል ሳትፈልግ የገባችበትን ጦርነት እየመከተች ሰፊ መዋዕለ ንዋይ በመመደብ እንዲሁም ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሰው ኃይል በማሠማራት ፈተናው በተሳካ ሁኔታ ሊከናወን መቻሉን ተናግረዋል፡፡

በዚህም ከ948 ሺህ ሦስት መቶ በላይ ተፈታኞች ተመዝግበው ከ937 ሺህ በላይ ተማሪዎች ወይም ከተመዘገቡት 98.8 በመቶ ለፈተና የተቀመጡ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡ በፈተና አስፈፃሚዎች ላይ ፈተና በሚሰጥበት ወቅት ቅሬታ ከሚቀርብባቸው ችግሮች ለማላቀቅ ፈታኞችን፣ ሱፐርቫይዘሮችን፣ ጣቢያ ኃላፊዎችንና አስተባባሪዎችን ከሥራና ትውልድ ቦታቸው ውጭ ወደ ሆኑ የፈተና ጣቢያዎች እንዲሠማሩ መደረጉንም ጠቅሰዋል፡፡

በሌላ በኩል የፈተናው ዝግጅትና ሕትመት ቀድሞ ከሚሠራበት ለመለየት በኮድ ብዛትና በገጽ አወቃቀር በመለየት ተማሪዎችና ወላጆች የፈተና ወረቀት ተሰርቋል ወይም አልተሰረቀም ከሚል ውዥንብር ለመታደግ ሁለቱ የትምህርት መስኮች 12 ኮድ እንዲኖራቸው እንደዚሁም መለያ ኮዱም ከሚታወቅበት ሁለት ኮድ ወደ ሶስት በመቀየር ከፈተና በፊት ከተለመደው ፈተና ደርሶናል ከሚል ማደናገሪያ መከላከል እንደተቻለ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ወደ ፈተና ዝግጅት የሚገቡ ባለሙያዎች የአካል ፍተሻና የ24 ሰዓት የደህንነት ካሜራ ጥበቃ በማድረግ ሥራው በከፍተኛ ጥንቃቄ ተመርቷል ብለዋል፡፡

መስከረም 30 በማኅበራዊ ሳይንስ ፈተና ወቅት በመጀመሪያው ቀን በሃዋሳ ዩኒቨርስቲ ከዋናው ግቢ ወደ ቴክኖሎጂ ግቢ ያለው የመተላለፊያ ድልድይ ወድቆ በ451 ተማሪዎች ላይ በደረሰው አደጋ ምክንያት ከፈተናቸው የተስተጓጎሉ ተፈታኞች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በሚዘጋጀው ፈተና እንዲወስዱ የሚደረግ ይሆናል ብለዋል፡፡

በማኅበራዊ ሳይንስ ፈተና ወቅት 12,993 ተማሪዎች አንፈተንም በማለት ጥለው የወጡ ተፈታኞችን በሚመለከት ደግሞ በመደበኛ ተማሪነት የመፈተን እድል የማይሰጣቸው ሲሆን በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በግላቸው መፈተን እንደሚችሉ ሚኒስትሩ አመልክተዋል፡፡

በፈተናው ያጋጠሙ ውስን ችግሮች ቢኖሩም በፈተና ዝግጅቱ፣ ስርጭቱና አሰጣጡ በከፍተኛ ደረጃ ስኬታማ ነበር ማለት እንደሚቻል ፕሮፌሰር ብርሃኑ ተናግረው፣በተለይም የፈተና መሰረቅና መውጣት አለማጋጠሙ፣ ሂደቱ በወጥነትና በከፍተኛ ሥነ-ሥርዓት መመራት መቻሉ፣ እንዲሁም በሁሉም አካላት ዘንድ በተገኘው ቅቡልነት ለትምህርት ሥርዓቱ አዲስ ጅማሮና መሠረት የጣለ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

በዚህ ፈተና የሚመዘገበው የፈተና ውጤት ተማሪዎች፣ ትምህርት ቤቶችና ክልሎች ያለባቸውን ጉድለት ለመረዳት፣ መፍትሔዎችንም ለመቀየስና በትምህርት ሥርዓቱ ያጋጠመውን ስብራት ለማከም ወሳኝ የታሪክ መታጠፊያ እንደሚሆን ጠቅሰዋል፡፡

## መከላከያ ሳይንስና ቴክኖሎጂን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዶክተር ሙላቱ፤ በመከላከያ ተቋሞቻችን ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ሉዓላዊነታችን የማስከበር ብቻ ሳይሆን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ራሱን ገንብቶ የዘርፉ ግኝቶች አመንጪ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ በአሁኑ ዘመን በስፔስ ሳይንስም ሆነ በሌሎች ዘርፎች ውስብስብ የሆኑ የሳይንስ ግኝቶች ምንጫቸው መከላከያ ነው፡፡

መከላከያ በሳይንስና ቴክኖሎጂው ዘርፍ ግንባር ቀደም ሚና በመጫወት ሀገራችን ወደሚፈለገው የብልጽግና ማማ ማስቀመጥ ይገባል፡፡ አሁን ላይ ውጊያው እንደድሮው በጦርና በጋሻ ሳይሆን በሳይንስና ቴክኖሎጂ በመሆኑ በዘርፉ መከላከያ ሰፊ ሥራ መሥራት አለበት ነው ያሉት፡፡

በመጽሐፉ ምረቃ መርሐ ግብር ንግግር ያደረጉት የመከላከያ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ማርታ ሉዊጂ፣ ለኢትዮጵያና ሕዝቦቿ የሚመጥን አስተማማኝ ዝግጁነት ያለው ሠራዊት እየተገነባ ይገኛል። አገርን ለማስቀጠል ሠራዊቱ እየከፈለው ያለው መስዋዕትነት በምንም ሊገለጽ አይችልም ብለዋል።

የመከላከያ ሠራዊት የጥንካሬ ምንጩ ሕዝቡ በመሆኑ በሕዝቡ ደጀንነት የሀገርን ሉዓላዊነት ያስከብራል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ የሀገርን ሉዓላዊነት ለማስከበር በየግንባሩ ለሚዋደቁ የሠራዊት አባላት ክብር ይገባል ብለዋል።

የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚመጥን ሠራዊት እየተገነባ ይገኛል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ ጦርነትን ተዋግቶ ማሸነፍ ብቻ ሳይሆን በፈጠረው አስተማማኝ ዝግጁነት ጦርነትን ከሩቅ ማስቀረት የሚችል አቅምና ዝግጁነት ያለው ሠራዊት ለመገንባት በሰፊው እየተሠራ ይገኛል፡፡

በመከላከያ ሚኒስቴር ጥናትና ምርምር ማዕከል የወታደራዊ ንድፈ ሐሳብ ጥናት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተርና የመጽሐፉ ዝግጅት ኮሚቴ ዋና አስተባባሪ ኮሎኔል ሙላት ደሳለኝ እንደገለጹት፤ የመከላከያ ሠራዊት ቀንን በማስመልከት "የእሳት ቀለበት" የተሰኘው መጽሐፍ ለማዘጋጀት አንድ ዓመት ከስድስት ወር የሚጠጋ ጊዜ መውሰዱን የገለጹት ኮሎኔሉ፤ መጽሐፉ በሦስት ምዕራፎች የተዋቀረ ነው ብለዋል።

ከሚያዝያ 20/2013 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ትግራይ ክልል በመሄድ በወቅቱ የነበሩ አራት ዕዞችን ያማከለ 11 መኮንኖች በማሠማራት ከሁሉም የጦር ክፍሎች መረጃ ከወታደር እስከ ከፍተኛው አመራር ድረስ መሰብሰብ መቻሉን ኮሎኔል ሙላት ገልጸዋል።

በሂደቱም ጦርነቱን የመሩ ከጄኔራል እስከ ኮሎኔል ማዕረግ ደረጃ ያላቸው 44 አመራሮችን በተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ መሠራቱን እና በጥቅሉ 1 ሺህ 685 ሰው የተሳተፈበት ውይይት ተደርጎ መረጃ መሰብሰብ መቻሉን ተናግረዋል። ሌሎች ተጨማሪ የመረጃ ምንጮችም እንደ ግብዓት ተወስደዋል። መጽሐፉ በርካታ የሠራዊታችን ውጣ ውረዶች፣ በሕወሓት ጁንታ ቡድን የደረሰበትን ክህደት ለምንና እንዴት እንደሆነ በሚያሳይ መልኩ ለአንባቢ የቀረበ ነው ተብሏል።

ስለመጽሐፉ አስተያየት ከሰጡት መካከል ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፤ ሕወሓት ገና በበረሃ እንዳለ በማኒፌስቶው አገር አፍራሽ የሆነ ዕኩይ ተግባሩን በማሳየት በድንገት የመጣ ሳይሆን ገና ከአፈጣጠሩ ጀምሮ በቀረጸው ማኒፌስቶ መሆኑን በሚያሳይ መልኩ ሰፊ ትንታኔ እንዲይዝ መደረጉ ለሌሎች የስነልቦና አጥኚዎች መነሻ ሊሆን የሚል ነው፡፡

ጁንታው አፈር ልሶ ተነስቶ እንደገና ወደ ለመደው የጦርነት አባዜው ለምን እንደተመለሰ፣ ሠራዊቱ የጁንታውን ጥቃት ማስፋፋት ለማስቆም ያደረጋቸውን ተጋድሎዎችና ከደብረሲና መልሶ እንዴት ትግራይ እንዳስገባው፣ በቅርቡ ሦስተኛ ዙር ጥቃት የከፈተበትንና ሠራዊቱን የወሰደውን መልሶ የማጥቃት ሂደት በየፈርጁ በመጻፍ በቁጥር ሁለት ለአንባቢያን ለማድረስ እየተሠራ መሆኑን ኰለኔሉ ተናግረዋል፡፡

## “መንግሥት እያደረገ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እና ከከፋ ችግር መታደግ ጠቃሚ መሆኑን የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ገለጸ፡፡

የፓርቲው ሊቀመንበር አረጋዊ በርሄ(ዶ/ር) በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤ መንግሥት በትግራይ ሰብዓዊ ድጋፍን ለማድረስ እና በአሸባሪው ትሕነግ የወደሙ መሠረተ ልማቶችን መልሶ ለመጠገን እያደረገ ያለው ሥራ ሕዝቡን ካለበት ሰብዓዊና ሥነልቦናዊ ጫና ለማላቀቅ የሚጫወተው ሚና የጎላ ነው፡፡

ዶ/ር አረጋዊ፣ የሀገር መከላከያ ሠራዊት ሕዝብን ለከፋ አደጋ ያጋለጠውን አሸባሪ ቡድን በመከላከል ክልሉን ወደ ሰላም እንደሚመልስ ሙሉ እምነት እንዳላቸውም ገልጸው፤ መንግሥትም እስከመጨረሻው ኃላፊነቱን በውል እንዲወጣም ጠይቀዋል ፡፡

እንደ ዶክተር አረጋዊ ገለጻ፣ ሕወሓት በአፉ ለትግራይ ሕዝብ እንደሚቆም ቢገልጽም በተግባር ግን ጠላቱ ነው፡፡ ቡድኑ ሲፈጽማቸዉ የቆየውን ፀረ-ትግራይ ሕዝብ ድርጊቶቹን ዛሬም ቀጥሎበታል ፡፡ የሕወሓት አመራሮች ድሃውን የትግራይ ሕዝብ ወደ ጎን በመተው በአዲስ አበባ ሰማይ ጠቀስ ፎቆችን ከመገንባት አልፎ ልጆቻቸውን ለትምህርትና ለሕክምና ወደ ውጪ ሀገር በመላክ የድሎት ኑሮ ሲኖሩ መቆየታቸውን የቅርብ ትዝታ ጊዜ ነው፡፡

የሽብር ቡድኑ ሰብዓዊ እርዳታ ሰጪና ከልካይ በመሆን ሕዝቡን በረሃብ የሰብዓዊ እርዳታ ጥገኛ በማድረግ ለካድሬው ታማኝና መብታቸው እንዳይጠይቁ በማድረግ ሕዝቡን ለግል ዓላማቸው ማስፈጸሚያ አድርጎ ሲጠቀምባቸው ቆይቷል ያሉት ሊቀመንበሩ፤ በሥልጣን ዘመኑ ተመሳሳይ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚዊ አፈናዎችን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ አድርሷል ብለዋል፡፡

በተለይ በአገሪቱ ወጣቶች ትግል ከስልጣኑ ተሽቀንጥሮ መቐሌ ለመከተም የተገደደው ቡድን ከተጠያቂነት ለመዳን ራሱን በማደራጀት የሀገር መከላከያ ላይ ጥቃት በመሰንዘር ሀገር ጦርነት ውስጥ እንድትገባ ማስገደዱንም አንስተዋል፡፡

ሕወሓት ለትግራይ ሕዝብ የሚላከውን ሰብዓዊ እርዳታ ለሠራዊት ቀለብ በማዋል ሕዝቡን በረሃብ እየቀጣ መሆኑን የጠቆሙት ሊቀመንበሩ፣ ሰብዓዊ እርዳታ ጭነው የመጡ 1 ሺህ 600 የሰብዓዊ እርዳታ ጫኚ መኪኖች እና በብዙ ሺህ ሊትሮች የሚቆጠር ነዳጅ በመዝረፍ ለወታደራዊ አገልግሎት በማዋል እርዳታው ለሕዝቡ እንዳይደርስ ማድረጉንም አውስተዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የትግራይ ወጣቶችን ለጦርነት እየማገደ ሕዝቡ በታሪኩ አይቶ በማያውቀው ሰቆቃ ውስጥ እንዲወድቅ አድርጓል ያሉት ዶክተር አረጋዊ፤ ጀግናው ሀገር መከላከያ ሠራዊት ሕዝብን ከነዚህ እና ከሌሎች ጠላቶች ለመከላከል እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ በማጠናከር የሕዝቡን የረሃብና የስነልቦና ጉዳት ማከሙን መቀጠል አለበት ብለዋል፤ ለዚህም ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ከመንግሥት ጎን እንዲቆም ጠይቀዋል ፡፡

እየተወሰደ ባለው እርምጃ ከአንዳንድ የውጭ ኃይሎች የሚሰሙ አላስፈላጊ ድምጾች የሽብር ቡድኑን ለማዳን የሚሰሙ ድምጾች መሆናቸውን የጠቀሱት ሊቀመንበሩ፤ ውድቀቱን በማረጋገጥ ጊዜን ለመግዛት ሰላም ፈላጊ መስሎ እየቀረበ ያለው ቡድንና ለጥሩ ተላላኪያቸው በሚጮኹ ሚዲያዎች ሳይገድብ የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል፡፡

## በመተከሉ “ስለ ኢትዮጵያ”...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሀብቷን በአግባቡ ሳትጠቀምበት ዘመናት ተቆጥረዋል። አገሪቷ ካሏት በርካታ እምቅ የተፈጥሮ ሀብቶቿ መካከል የውሃ ሀብቷ ተጠቃሽ ነው ያሉት ኢንጂነር ክፍሌ፤ የአባይ ተፋሰስ ብቻ 70 በመቶ የአገሪቷን የውሃ ሀብት የያዘ ነው ብለዋል።

በአባይ ተፋሰስ ውስጥ ያሉ ወንዞችን ጨምሮ የኢትዮጵያ አብዛኛዎቹ ወንዞቿ ከከፍተኛ ቦታ የሚፈሱ በመሆናቸው በተለይ ለኤሌክትሪክ ኃይል የሚውሉ ቢሆኑም ሀብቱን በአግባቡ አሟጥጦ መጠቀም አለመቻሉንም ነው የገለጹት፡፡

ኢትዮጵያ ከውሃ ብቻ 45 ሺህ ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ትችላለች፤ ከዚህ ውስጥ ደግሞ 67 በመቶው ከአባይ ተፋሰስ የሚገኝ በመሆኑ ይህንን ተፋሰስ ማልማት ትልቅ ሀብት መፍጠር ነው፤ የመኖር እና ያለመኖር ጉዳይም ነው ብለዋል ኢንጂነር ክፍሌ።

አብዛኛዎቹ ወንዞች ድንበር ተሻጋሪ በመሆናቸው ሀገራቱ ፋይናንስ እንዳይገኝ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ ይሄም ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ሀገራት የውስጥ ጉዳያችን ውስጥ ገብተው የተልዕኮ ጦርነት እያደረጉብን ነው ያሉት ኢንጅነር ክፍሌ፤ ኢትዮጵያ ይሄንን ተቋቁማ ፕሮጀክቷን ከዳር እያደረሰች ትገኛለች ብለዋል።

"የምንሠራው የዓባይ ግድብ ለአፍሪካ ሞዴል የሆነና መንገድ ያሳየ ፕሮጀክት ነው"፡፡ ለአፍሪካ ወንድሞቻችን መንገድ እያሳየን ነው፡፡ የተጀመሩ ውጥኖቻችን ይቀጥላሉ። ግድባችን ሥራው በከፍተኛ ቁርጠኝነት እየተገነባ ነው ብለዋል፡፡

የግድቡ አጠቃላይ ግንባታ ከ86 ነጥብ ሶስት ከመቶ በላይ መድረሱን፣ ሁለቱ ተርባይኖች ኃይል እያመነጩ እንደሚገኙም ኢንጂነር ክፍሌ ተናግረዋል፡፡

በኮንክሪት ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያውያን ደም ጭምር እየተገነባ ያለውን ፕሮጀክት "በቦንብ ማፍረስ ይቻላል" የሚል ዛቻ ሳይቀር የተሰነዘረበት፤ የግንባታ ግብዓት እንዳይደርስ መንገድ ላይ ማስተጓጎል የተካሄደበት፣ ሲሚንቶ እንዳይመረትም ፋብሪካው አካባቢ የሽብር ሥራ የተሠራበት ቢሆንም በመንግሥት ጥረትና በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ርብርብ እዚህ ደርሷል ብለዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ መምህር እና የአባይ ውሃ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ያዕቆብ አርሳኖ በበኩላቸው ባቀረቡት የመወያያ ጽሑፍ፤ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ብዙ አገሮች በጦርም፣ በገንዘብም በሃሣብም በርካታ ጥረት ቢያደርጉም ኢትዮጵያ ጸንታ መቆሟን አመልክተዋል፡፡ እንደውም አንዳንዶቹ እራሳቸው መፍረሳቸውን ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ ጥንታዊት ሀገርና የመንግሥት ታሪክም ያላት ሀገር ናት ያሉት ዶክተር ያዕቆብ፤ አገዛዝ ይለወጣል፤ ይሻሻላል ይህንን እውነታ በመረዳት ሀገርን በዘላቂ ሰላም ማሻገር እንደሚገባና ያለው እድል ኢትዮጵያን ማልማትና ማሣደግ ብቻ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ አንድነት በብዙ ዋጋ የተገኘ በመሆኑ አንድነትን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባም አብራርተዋል። ሰላም የሁሉም የጋራ ጉዳይና በየዘመኑም የሚገነባ እሴት ነው ሲሉም ተናግረዋል፡፡

መልካም አስተዳደርንም ማስፈን ካልተቻለ ዘላቂ ሰላም ሊመጣ አይችልም፣ ሰላምን ስንፈልግ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥም ይገባል ሲሉም አመልክተዋል፡፡ ኢትዮጵያ ለራሷ ነጻነት ብቻ ሳይሆን ለተቀረው ዓለም ነጻነት ምሳሌ መሆን የቻለች አገር መሆኗንም ዶክተር ያዕቆብ አስታውሰዋል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሀብት የታደለች ሀገር ናት፡፡ ይሄንን ሀብት በአግባቡ፣ በወንድማማችነትና በመከባበር መጠቀም ይገባል፤ ዜጎች በእኩልነት የሚኖሩባት፤ ያልተገደበ ነጻነት ያለባት፤ በጎጥ ያልተገደበ ተጠቃሚነት የሰፈነበት አገር ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡

አቶ አሻድሊ ሀሰን ባቀረቡት የማጠቃለያ ሃሳብ እንደተናገሩት፣ ለሀገር አንድነትና ተጠቃሚነት መረጋገጥ ሁሉም አርበኛ ሊሆን ይገባል ብለዋል።

ይሄ አገር ከፍተኛ መስዋዕትነት በየዘመኑ ተከፍሎበት እዚህ የደረሰ ነው ያሉት አቶ አሻድሊ፤ ኢትዮጵያውያን የምንታወቅበትን ነጻ ሕዝብነት በድህነትም ልንደግመው ይገባል፤ ለዚህም የተጀመሩ የግብርና እና የአረንጓዴ አሻራ ሥራዎችን ማጠናከር ይጠበቅብናል ሲሉ አብራርተዋል።

በተለይ ባለፉት አራት ዓመታት ብዙም ሳይነገር በግብርናው መስክ ብዙ ተሠርቷል፤ብዙ ጥረት ተደርጓል፤ በዚህም ከእኛም አልፎ ለቀጣናው ሀገራት የሚተርፍ ውጤት እየተመዘገበ ይገኛል፤ ይህንን ውጤታማነት ተከትሎም ብዙ ፈተና በዝቷል፤ ይህ የሆነው ደግሞ ራሳችንን እንቻል፤ ነጻም እንውጣ የሚል መንገድ ስለተጀመረ ነው ሲሉም ነው ያብራሩት።

ብዙ ሀገሮች አቅጣጫ ያስቀምጣሉ፣ ይነድፋሉ፤ ነገር ግን የሚያሳኩት በጣም ጥቂት ነው፤ በኢትዮጵያም ላለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት ስለ ግብርና፤ ስለ ኢንዱስትሪ ያልተነገረ ነገር የለም፤ ነገር ግን ተጨባጭ ለውጥ የታየው በዚህ አራት ዓመት ውስጥ ነው ብለዋል አቶ አሻድሊ።

በስንዴ ልማት፣ በማዕድን፣ በቱሪዝም የተጀመረው ሥራ ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና ያሻግራል፤ ከዚሁ ባልተናነሰም የአገልግሎት ዘርፉን ማዘመንና ማጎልበት ያስፈልጋል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሠራዊቱ አኩሪ የተጋድሎ ታሪክ መጭው ትውልድ ለዘለዓለም የሚያከብረውና የሚያወድሰው ነው!

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከፍ ባለ ተጋድሎ የሃገርን ሕልውና በማስከበር ሕዝብና መንግሥት የጣለበትን ሕገ መንግሥታዊ ኃላፊነት በብቃት በመወጣት ላይ ይገኛል። ሃገርን አበቃላት ከሚል የጠላቶች ሟርት በሚያስደምመው የግዳጅ አፈጻጸሙ ታድጓል እየታደገም ይገኛል።

በሃገር ሉዓላዊነት የመደራደር ታሪክ ከሌለው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብራክ የወጣው ይህ ሠራዊት የተቃጣበትን የክህደት ጥቃት ተቋቁሞ ፤ላለፉት ሁለት ዓመታት ከአሸባሪው ትሕነግ ጋር ሀገርን ከውድቀት ፤ ሕዝብን ከመበተን መታደግ የሚያስችል ግዳጅ ውስጥ ይገኛል።

አሸባሪው ትሕነግ በሃገርና በሕዝብ ላይ ከአንዴም ሁለት ሦስቴ የቀሰቀሰውን የእብሪትና የውክልና ጦርነት ሕዝባዊነቱን መሠረት ባደረገ ከፍተኛ ጥንቃቄ በማክሸፍ ፤ ለሀገር ሉዓላዊነት፣ ለሕዝቦች አንድነት እና ሰላም ያለውን ክብር በአኩሪ መስዋዕትነት በማጽናት ላይ ይገኛል።

ሠራዊቱ በአንድ በኩል ሀገርን የማዳን የሕልውና ጦርነት ከአሸባሪው ትሕነግ እና ከሌሎች አሸባሪና ጽንፈኛ ቡድኖች ጋር እያካሄደ፤ በሌላ በኩል ተተኪ ኃይል በጥራትና በብዛት በማሰልጠን ፤ሀገሪቱ መቼም ቢሆን የጀግና መሐን ሆና እንደማታውቅ በተጨባጭ አስመስክሯል።

መንግሥትም የመከላከያ ሠራዊቱን በዕውቀት ፣ በክህሎትና በቴክኖሎጂ ለማዘመን ላለፉት ሁለት ዓመታት ያካሄዳቸው የሪፎርም ሥራዎች በሠራዊቱ የግዳጅ አፈጻጸም ላይ በግልፅ የሚታይ ለውጥ አምጥቷል። በሠራዊቱ ሕዝባዊነት ላይም የጎላ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

ሠራዊቱ በእነዚህ ሁለት ዓመታት ጀግና የመከላከያ ኃይል በማፍራት፤ መቼም እና የትም ግዳጅን በብቃት እና በጀግንነት መወጣት የሚያስችል ሕዝባዊ ወገንተኝነት ያለው ሠራዊት መፍጠር የሚያስችል ተቋም ሆኗል። በዚህም ለሃገርና ለሕዝብ የኩራት ምንጭ ሆኗል።

ይህ የሠራዊታችን አኩሪ እውነታ ወዳጆቻችን ደስ አሰኝቷል፤ ጠላቶቻችን ደግሞ ስለ ኢትዮጵያ የሚያስቡትን ነገር ሁለት እና ሦስት ጊዜ ቆም ብለው እንዲያስቡ አስገዳጅ ሁኔታ መፍጠር አስችሏል። የሠራዊቱ አባላትም የሠራዊቱ አባል በመሆናቸው እጥፍ ድርብ ክብር እንዲሰማቸው አድርጓል።

የመከላከያ ሠራዊቱ ሀገርን ከጥፋት ፤ሕዝብን ከመበተን እየተከላከለ የመጣበት የተጋድሎ መንገድ ትውልዱ በራሱ ዘመን በአኩሪ መስዋዕትነት የራሱን ታሪክ በመሥራት የአትንኩኝ ባይነት የቀደመ ታሪኩን እንዲያድስ የተሻለ መደላድል ፈጥሯል። በዚህም ሀገሪቱ ዛሬም የጀግኖች እናት መሆኑዋን በተግባር አስመስክሯል።

በእያንዳንዱ እንቅስቃሴው ከፍተኛ የሕዝብ አመኔታ እያተረፈ ያለው የመከላከያ ሠራዊታችን ፤ይህ የሕዝብ አመኔታው ለእያንዳንዱ የግዳጅ አፈጻጸሙ አቅም በመሆን በራስ የመተማመን መንፈሱን አሳድጎለታል፤ በቀጣይም ለሃገራዊ የሠራዊት ግንባታ የተሻለ መደላድልና አቅም እንደሚሆንለትም ይታመናል ።

ሠራዊቱ እንደቀድሞው ዛሬም ላይ ብዙ ሟርቶችን ቀልብሶ የኢትዮጵያ ደጀንና መከታ መሆኑን ደግሞ እያረጋገጠ ይገኛል። ወደዚህ የታሪኩ ምዕራፍ ላይ ለመድረስ የከፈለው ዋጋ ከፍ ያለ እውቅና እና ከበሬታ የሚለገሰው ፤ በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥም የደመቀ ብርሃን ሆኖ በወርቃማ ቀለም የሚጻፍ ነው።

በተለይም ሃገርና ሕዝብ አደጋ ላይ መሆናቸውን ተገንዝበው ከሀገሬ በፊት እኔ ልቅደም በሚል ጨርቄን ማቄን ሳይሉ ሠራዊቱን በመቀላቀል በተለመደው ኢትዮጵያዊ ጀግንነት በሕይወታቸው መስዋዕትነት የሃገር ሰላምና ዜጎች ደህንነት አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ላደረጉ የሠራዊቱ አባላት በሙሉ ኢትዮጵያ በትልቁ ታከብራቸዋለች።

ከሃዲዎችና ባንዳዎች ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ጋር አብረው ፣ በእብሪትና በማን አለብኝነት በሃገርና በሕዝብ ላይ ደቅነውት የነበረውን የሕልውና አደጋ በመቀልበስ እንደ ሕዝብ ስለነገ ተስፋ ያደረግናቸውን የተስፋችንን ፍሬዎች ማየት የሚያስችለንን ዕድል ስለፈጠሩልን ለእነዚህ የሠራዊቱ የቁርጥ ቀን ልጆች የሚቀርበው ምስጋና ከቋንቋ በላይ ከፍ ያለ ነው!

እነዚህ የዚህ ትውልድ ጀግኖች ስለሃገር እና ስለሕዝብ የከፈሉት መስዋዕትነት የነገ ተስፋችን ተቋዳሽ የሆኑ ትውልዶች በሙሉ ለዘለዓለም የሚያስቡት ፤የሚያከብሩትና የሚያወድሱት ሕያውና አኩሪ የመስዋዕትነት ታሪክም ነው!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73
ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# በቃላት የማይገለፁት የዶክተሩ ስህተቶች

ግርማ

የአፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽምና አየር ላይ ከዋለ ዋለ እንጂ እንዳልዋለ ማድረግ ከማንም ሰብአዊ ፍጡር አቅም በላይ ነው። በመሆኑም፣ ዛሬ ዶክተሩ ይይዙ ይጨብጡትን ቢያጡ፤ ባሉት፣ ባወሩት፣ በዋሹና በቀባጠሩት ቢፀፀቱና ቢንገበገቡ ጉዳዩ የፈሰሰ ውሀ ነውና እዳው ገብስ አይደለም።

ዶ/ር ቴዎድሮስ አድሀኖም በአሁኑ ሰዓት የዓለም ጤና ድርጅት ዳይሬክተር ናቸው። በመሆናቸውም መቀመጫቸው ጄኔቭ ይሆን ዘንድ ግድ ብሏል። ማለትም ጄኔቭ ናቸው ማለት ነው።

ዶክተሩ ጄኔቭ ይሁኑ እንጂ እየሠሩት ያለው ግን የጄኔቩ ወንበራቸው የሚፈልገውን ተግባርና ኃላፊነት ሳይሆን የበረሃው ምሽግ የሚፈልገውን ነው። እሚመሩት በጤና ድርጅቱ ሕግና ደምብን ሳይሆን በደደቢት ማኒፌስቶ ይመስላል። በመሆኑም ጉዳዩ ለዓለም ችገር ብሎ ይገኛል።

ሰውየው፣ በተለይም በአሁኑ ሰዓት እየፈፀሙት ባለው ስህተታቸው ምክንያት ከኢትዮጵያውያን ጋር ብቻ አይደለም፤ ከሰላም ወዳዱ የዓለም ማኅበረሰብ ጋር ሁሉ ነው የተጋጩት። «ወደጃችን» ከሚሏት አሜሪካ ጋር ሳይቀር ተላትመዋል (ሕወሓት ጎጠኛ፣ ሙሰኛ፣... ድርጅት መሆኑን እና መቀጠል የሚገባው ድርጅት አለመሆኑን በመግለፅ አስተያየታቸውን በቲውተር ገፃቸው ላይ ያሰፈሩትን የኸርማን ኮኸንን አስተያየት ልብ ይሏል)።

የአፍሪካ መሪዎች ተበሳጭተውባቸዋል። ዓለም አቀፍ ተቋማት የሰውየውና ድርጅታቸው ነገር ቆርጦላቸዋል። እነ ዩኤን ሳይቀሩ የሰውየው መረን የለቀቀ አስተያየት በሕግ እንዲታይና ውሳኔ ላይ እንዲደረስ ስምምነት ላይ ደርሰዋል። እየደረሰባቸው ያለው ብዙ ... ብዙ ነው።

እስኪ ትንሽ ወዳ ኋላ ሄደን ስለ ዶክተሩ ሰብእና ጥቂት እንበል።

በቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ አስተዳደር ዘመን ቻይና አፍሪካ ውስጥ እያደረገች ያለችውን የኢኮኖሚና የፖለቲካ መስፋፋት ያሳሰባት አሜሪካ «ምነው ምን አድርገናችሁ ነው ፊታችሁን ያዞራችሁብን?» ለማለት የሚመስል ስብሰባ ለማካሄድ በርከት ያሉ የአፍሪካ መሪዎችን ቤተ መንግሥቷ ድረስ ጋብዛ ነበር።

በዚያ «የሃሳብ ልውውጥ»፤ «ምክር»፤ «ምክክር» ምንትሴ ... በተባለው ስብሰባ ላይ (የእራት ግብዣና የዋሺንግተን ዲሲን ጉብኝትን ጨምሮ) ድግስ ላይ በመልካም የዴሞክራሲ ጅምራቸው የሚወደሱት የጋናና የደቡብ አፍሪካን መሪዎች ጨምሮ፣ ጠ/ሚ ደሳለኝ ኃ/ማርያምን አጅበው የሄዱት የያኔው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቴዎድሮስ አድሀኖም ተገኝተው ነበር። ችግሩ መገኘታቸው አይደለም፤ ችግሩ መናገራቸው ነው።

ሰውየው በዲሲ ቆይታቸው ወቅት ብዙዎችን፣ ሰነባብቶም ራሳቸውን ያሳፈረ ቃለ መጠይቅ መንግሥታቸው ከደሀ ጉሮሮ ቀንሶ የአየር ላይ ወጪ እየከፈለ ሲያስተዳድረው ከነበረ ሬድዮ ጋር አድርገው ነበር። ነገሩ አፍ ሲያመልጥና ራስ ሲመለጥ አይታወቅም ሆነና በቃለ መጠይቁ ወቅት የተናገሩትን አዲስ አበባ ከተመለሱ በኋላ በፌስቡክ ገፃቸው ሊያስተባብሉ ቢሞክሩም ሳይቻላቸው ቀርቶ እነሆ «ታግ» ሆኖ (ዕድሜ በወቅቱ ሀሳቡን ላጋሩን ኤፍሬም ማዴቦና ለመሳሰሉት) እስከዛሬዋ ዕለት ድረስ ዘልቆ እየጠቀስነው እንገኛለን።

ዶክተሩ «ሬድዮ አገር ፍቅር» በሚል ከሚታወቀው ሳምንታዊ ሬድዮ ጣቢያ ጋር ባደረጉትና፣ በተለይም ዲያስፖራውን ማህበረሰብ ባስቀየመው ቃለ ምልልሳቸው፤ «በእስር ላይ የሚገኙት የድምጻችን ይሰማ መሪዎች የአሜሪካ መንግሥት ጓንታናሞ ውስጥ ካሠራቸው የአልቃይዳ አባላት ጋር ግንኙነት እንዳላቸው ማረጋገጫ አግኝተናል»፤ «የአሜሪካ መንግሥት ይህንን ግንኙነት አስመልክቶ የድምጻችን ይሰማ መሪዎችን ኢትዮጵያ ድረስ ሄዶ ለማነጋገር ለመንግሥታችን ጥያቄ አቅርቧል» ... ነበር ያሉት።

በወቅቱ፣ ይህንን ንግግራቸውን ተከትሎ እሳቸው ብቻ ሳይሆኑ እሳቸው በአባልነት የሚገኙበት ትህነግ የሚባለው ድርጅት ሃያ ሦስት አመት ሙሉ እየዋሸ የዘለቀ ድርጅት መሆኑ ከበቂ በላይ ሲነገር ነበር የቆየው። ግማሽ ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ሁለት ቱባ ቱባ ውሸቶችን በመዋሸታቸው ምክንያት በወቅቱ የቀለሉት እሳቸው ብቻ ሳይሆኑ በእሳቸው አማካኝነት ፓርቲያቸውም ጭምር ነበር የስም ስብራት የደረሰበት።

ለዚህ፣ ለእሳቸው የአፍ ወለምታ አቢይ ምክንያት እሳቸው ብቻ ሳይሆኑ የኖሩበት ድርጅት መሠረታዊ ባህርይ መሆኑም ነበር በወቅቱ አየር ላይ ይውል የነበረው። «ያዲያቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም» እንዲሉ ሆነና እነሆ ያ የአፍ ወለምታ ዛሬም ድረስ አብሯቸው ኖሮ ለዳግም ቅሌት ዳርጓቸው ይገኛሉ።

ችግሩ ቅሌቱ አይደለም። የአሁኑን ለየት የሚያደርገውና ችግሩን ከመቅለልም በላይ ይሆን ዘንድ የሚያስገድደው ጉዳያቸው ወደ ሕግ የማቅናቱ ጉዳይ ነው። አዎ፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን አቤት ብለዋል። «ባፍ ይጠፉ፣ በለፈለፉ» ነውና በለፈለፉት ጉዳይ ሊጠየቁ ይገባል እያሉ ናቸው። ሰላም ወዳዱ የዓለም ሕዝብም ከኢትዮጵያና ኢትዮጵያውን ጎን መሆኑን ማህበራዊ ሚዲያውን ያጥለቀለቁት አስተያየቶች እያመላከቱ ነው።

እንደሚታወቀው፣ ፓርቲያቸው በአሁኑ ሰዓት የለም። አለ ከተባለ እንኳን «ከመቆሙት በታች፣ ከሞቱት በላይ» የሚባለው ዓይነት ነው። ይሁን እንጂ፣ ዶ/ር ቴዎድሮስ አድሀኖም ያንን የሚያክል ወንበር ላይ ቁጭ ብለው፤ በኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ስም እዛ ወንበር ላይ ፊጥ ብለው፣ ድፍን የዓለምን ሕዝብ ወክለው፤ የታመመውን ሊያድኑ፤ ያልታመመውን ሊከላከሉ ምለው ተገዝተው እያሉ፤ የዘሬን ብተው ይዘርዝረኝ ሆኖባቸው የሌለ ድርጅታቸው ዳግም ሊያኖሩ በማሰብ ከድፍን ዓለም ጋር ተጋጩ።

«ከማንም ጋር አንወግንም፤ የቆምነው ለእውነት ብቻ ነው» የሚለውን የሬዲዮ ጣቢያ ከአድማጮቹ ጋር ያቆራረጡት ዶክተሩ በወቅቱ «የኢትዮጵያን የእስልምና እምነት ተከታዮች ከአልቃይዳ ጋር ማገናኘት እነዚህ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ያነሱትን ሕጋዊ የመብትና የነፃነት ጥያቄ ላለመመለስ የሚደረግ አጉል ውጣ ውረድ» እንደሆነ ሲሰነዘሩባቸው ከነበሩት ትችቶች መካከል አንዱ ሲሆን፤ ሰውየው ከልምድም ይሁን ከሕይወት የመማር ልምድ አልታደሉምና ዛሬም እዛው ተገኙ።

የዛን ጊዜው ቅጥፈትና የራስን ወገን ከአልቃይዳ ጋር ማዛመድ ዋናው ምክንያቱ «ወዳጃችን» የሚሏትን አሜሪካንና የኦባማን አስተዳደር ማስደሰት ነበር። የአሁኑ፣ ምንም ሳይታክቱ፣ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ፣ ያለ ምንም እፍረት (ካፈርኩ አይመልሰኝ በማለት ይመስላል) «በትግራይ ዘር ማጥፋት እየተካሄደ ነው ...» ማለታቸው ደግሞ፣ መቀመጫቸውን ጄኔቭ (ስዊዘርላንድ)፣ መተማመኛቸውን አሜሪካ አድርገው ሲሆን፤ ምክንያቱ ደግሞ ከወከሉት ዓለም አቀፍ ወንበር ወደ ጎጥ የመንከባለል አባዜ ነውና በአንድ በኩል ሰውየው ያሳዝናሉ።

ሰውየው በዚህ ብቻም ያበቁ አይደሉም። ሁሌም ከትህነግ በላይ ትህነግ ከመሆን ቦዝነው አያውቁም። ያለመቦዘናቸው ማሳያም ባለፈው ኦገስት መግቢያ ላይ «ምዕራብ ትግራይ (ወልቃይት)ን ነፃ ለማውጣት እንገደዳለን!!» በማለት የዓለም ጤና ድርጅት ዳይሬክተርነታቸውን ትተው የውጊያው ፊት መሪ ሆነው መገኘታቸው ነው።

በመጨረሻም፣ «በቃላት የማይገለፁት የዶክተሩ ስህተቶች» በሚል ርእስ የጀመርነውን (ወደን ሳይሆን የአገር ክህደት ተግባራቸውን በቃላት መግለፅ አስቸጋሪ በመሆኑ ነው) ጽሑፋችንን እዚሁ ላይ እናቁም። ስናቆም ግን ጉዳዩ በዓለም አቀፍ ሕግ በመያዙ ምክንያት ወደ ዝርዝር ጉዳያቸው፣ ጥልቅ ስህተታቸው፤ አገርና ሕዝብ ክህደታቸው ... ባለመግባት፤ ለጊዜውም ቢሆን በመታገስ ነው።

## ፍረዱኝ

# ያልተከፈለ የጡረታ አበል - ለ11 ዓመታት

**ምሕረት ሞገስ**

አዛውንቱ በየቢሮ መንከራተት እንዳሰለቻቸው የፊታቸው የድካም ገጽታ ይናገራል። በድካም የዛለው ጉልበታቸው ይንቀጠቀጣል። የአይናቸው ብሌን ደብዝዞ ደም ለብሷል። አይኖቻቸው እምባ እንዳያፈሱ የድካም ዓይናር ገድቧቸዋል። ብዙ ተንከራተው መፍትሔ ስላጡ ወደ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል በመምጣት ለዓመታት ሲንከራተቱ መኖራቸውን ሕዝብ እንዲያውቅላቸው አስበው መገኘታቸውን በመግለፅ ተበደልኩ ያሉትን እንዲህ ሲሉ ገልፀዋል፡፡

**የአቤቱታው ፍሬ ነገር**

አቶ ገበየሁ ወልደሰንበት አሁን ስማቸውን በፍርድ ቤት ቀይረው አቶ ጉራቻ ሰንበቶ ቆሪቻ ተብለዋል። በአዲስ አበባ ከተማ ውሃ ክፍል ተብሎ ይጠራ በነበረው ተቋም፤ በመቀጠል በቀድሞ አጠራር በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት አገልግለዋል። ከዚያም ከ1987 ዓ.ም እስከ 1994 ዓ.ም ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ ፋይናንስ ቢሮ አገልግሎት የሰጡ ቢሆንም፤ ተገቢውን የጡረታ አበል ሳያገኙ 11 ዓመታትን እንዳሳለፉ ይገልፃሉ።

በ1994 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በወቅቱ በዞን 4 ፋይናንስ ቢሮ በቋሚ የመንግሥት ሠራተኝነት ሲያገለግሉ አንድ ደብዳቤ ደረሳቸው። ደብዳቤው በግንቦት 2 ቀን 1994 ዓ.ም የተፃፈ ሲሆን፤ ‹‹በጡረታ ልትሰናበት በመሆኑ የመንግሥት ንብረት አስረክብ፤ ያልተጠቀምክበትን የዓመት ዕረፍት ተጠቀም።›› የሚል ነበር።

እንደእርሳቸው ገለፃ፤ ይህ ከሥራቸው በጡረታ እንዲገለሉ የሚያመላክተው ደብዳቤ ጊዜውን የጠበቀ አልነበረም። ይህ ድርጊት የተፈፀመባቸው በወቅቱ ከነበረው የመስሪያ ቤቱ አስተዳደር ጋር አለመግባባት በመፈጠሩ እንጂ ዕድሜያቸው ደርሶ፤ ወይም ‹‹ጡረታ መውጣት እፈልጋለሁ›› ብለው በመጠየቃቸው አልነበረም። ስለዚህ የጡረታ መውጫ ደብዳቤ ስለተሰጣቸው ተቃወሙ።

ይህን ተከትሎ የጡረታ ጊዜዎ በመድረሱ ያልተጠቀሙበትን የዓመት ፍቃድ እንዲጠቀሙ እና ሥራዎትን እንዲያስረክቡ በሚል በድጋሚ ተጠየቁ። እርሳቸው በበኩላቸው የጡረታ መውጫ ጊዜያቸው እንዳልደረሰ የተቀጠሩበት ዘመንን በመግለጽ ተከራከሩ። አቶ ጉራቻ ባቀረቡት ሰነድ ላይ እንደተመላከተው በተቋሙ ቅጥር ሲያካሂዱ በሚያዝያ 11 ቀን 1968 ዓ.ም በሞሉት የሕይወት ታሪክ ፎርም መሠረት ግንቦት 30 ቀን 1994 ዓ.ም የጡረታ መውጫ ጊዜያቸው መሆኑን በመጥቀስ ‹‹ ጡረታ መውጣት አለብህ›› በማለት ደጋግሞ አሳሰባቸው።

አቶ ጉራቻ ግን በጡረታ ከሥራ መገለል በሚለው ሃሳብ ላይ በፍፁም አልተስማሙም። ተቋሙ በበኩሉ ‹‹ጡረታ መውጣት ግዴታዎት ነው›› ብሎ ወደ ቢሮ እንዳይገቡ ከለከለ። በወቅቱ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለዞን 4 ፋይናንስ ጽሕፈት ቤት በጽሑፍ አቤቱታ አቀረቡ፡፡

**ለዞን 4 ፋይናንስ ጽሕፈት ቤት የቀረበው አቤቱታ**

‹‹የተወለድኩት ሰኔ 16 ቀን 1940 ዓ.ም መሆኑን ለረዥም ጊዜ በማህደሬ ተያይዟል። ይህ በመሆኑም ጡረታ እንድወጣ የተሰጠኝ ደብዳቤ ሆን ተብሎ እኔን የግል አመልካቼን ለመበደል ታስቦ የተደረገ እንጂ የጡረታ መውጪያ ጊዜዬ ገና ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን ደብዳቤ ሳይደርሰኝ የደመወዝ መቁረጥ፤ በማይመለከተኝ ስብሰባ ላይ አልተገኘህም በሚል የደመወዝ ቅጣት ተወስኖብኝ ተግባራዊ ተደርጎብኛል።

አለቆቼ ከእነርሱ ጋር አለመተባበሬን እያስወሩ በሕጋዊነት ሽፋን ጊዜን እና ሁኔታን ተገን በማድረግ ግፍ እና በደል በመፈፀም መብቴን እና የሥራ ነፃነቴን ገድበውብኛል። ስለዚህ መብቴም ይከበር፤ የተቆረጠብኝ ገንዘብ ይመለስልኝ፤ የተሰጠኝ የጡረታ ውጣ ደብዳቤም ይሰረዝልኝ፡፡›› ሲሉ አቤቱታ ማቅረባቸውን ለዝግጅት ክፍሉ ያቀረቡት ሰነድ ያብራራል።

እንደ አቶ ጉራቻ ገለፃ፤ አቤቱታ ቢያቀርቡም ተገቢውን ምላሽ የሚሰጣቸው አካል አላገኙም። ስለዚህ ሕግ ይፈፀማል፤ ፍርድ አገኛለሁ ብለው በማመናቸው ጉዳያቸውን ይዘው ፍርድ ቤት ቀረቡ። ከጊዜው አስተዳደር ጋር የነበረውን አለመግባባት በሚመለከት፤ ይፈፀምባቸው የነበረውን በደል እና ግፍ እንዲሁም ደመወዝ እስከ መቁረጥ የደረሰ በደል እንደነበረባቸው አመልክተው፤ መስከረም 7 ቀን 1995 ዓ.ም ለፌዴራል



ፎቶ፡ ጸሀይ ንጉሤ

አቶ ጉራቻ ሰንበቶ ቆሪቻ

የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መናገሻ ምድብ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮን ከሰሱ።

**በ1995 ዓ.ም ያቀረቡት ክስ ጭብጥ**

ተቋሙ ማለትም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዞን 4 ፋይናንስ ጽሕፈት ቢሮ በወቅቱ 641 ብር ከ92 ሳንቲም ያለአግባብ ከደሞዛቸው የቆረጠ መሆኑን በመጥቀስ፤ ፍርድ ቤቱ ገንዘቡን እንዲያስመልስላቸው ጠየቁ። ጨምረውም ‹‹ጡረታ ወጥተሃል፤›› በሚል የሠራተኞች የሰዓት ፊርማ ላይ ቢፈርሙም ከሥራ እንደሌሉ ተቆጥሮ የተሰረዘ መሆኑን፤ ይህንንም የተሰረዘውን የሰዓት ፊርማ በማየት ማረጋገጥ እንደሚቻል በመጠቆም፤ የጡረታ መውጫ ጊዜያቸው አለመድረሱን በማመላከት ክስ አቀረቡ። ሆኖም ተቋሙን መርታት አልቻሉም።

እርሳቸው እንደሚገልፁት፤ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በትክክል መብታቸውን ባላገናዘበ መልኩ ውሳኔ አስተላለፈ። በዚህ ምክንያት ጡረታቸውንም ደሞዛቸውንም ሳይቀበሉ ተቋሙ ጋር እየተመላለሱ ሲንገላቱ ቆዩ። አቶ ጉራቻ ቀድሞ ጡረታ መውጣት የለብኝም እና ሌሎችም የአስተዳደር በደል ደርሶብኛል የሚሉ ጉዳዮችን በማካተት ተቋሙን ሲከሱ የቆዩት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ላይ ብቻ አልነበረም፤ በመቀጠል ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዞን 4 ፋይናንስ ጽሕፈት ቤትን በድጋሚ ይግባኝ በማቅረብ ከስሰዋል። ሆኖም ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቶት ነበር።

አቶ ጉራቻ አላቆሙም ‹‹ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መብቴን በትክክል ያላገናዘበ ነው፡፡›› በማለት፤ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቀረቡ። በዚህ ጊዜ በታህሳስ 2 ቀን 2004 ዓ.ም ለእርሳቸው ተወሰነላቸው። ከተወሰነላቸው በኋላ ግን አፈፃፀም እየተካሄደ እያለ ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት እራሱ አንድ አመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ የሰጠው ፍርድ በማገዱ፤ ደረጃውን ጠብቀው በይግባኝ እንዳያንቀሳቅሱ ያገዳቸው መሆኑን አስታውሰዋል።

ከዓመታት በኋላ ይሠሩበት የነበረው ተቋም ማለትም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዞን 4 ፋይናንስ ጽሕፈት ቤት ወደ ሌላ ቦታ ተዘዋወረ። ከዘጠኝ ዓመት በኋላ ለአራዳ ክፍለ ከተማ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽሕፈት ቤት ማመልከቻ አስገቡ።

**በ2003 ዓ.ም የቀረበ ማመልከቻ**

አቶ ጉራቻ ባቀረቡት ሰነድ በ2003 ዓ.ም ለአራዳ ክፍለ ከተማ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽሕፈት ቤት ማመልከቻ አቅርበዋል። ማመልከቻው የደረሰባቸውን በደል የሚዘረዝር እና ካሳ እንዲከፈላቸው የሚጠይቅ ነበር። በጽሕፈት ቤቱ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ከወረዳ 8 ማዘጋጃ ቤት በዝውውር መምጣታቸውንና ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ ግንቦት ወር 1994 ዓ.ም ድረስ በቅንነትና በታማኝነት ሲያገለግሉ መቆየታቸውን ያብራራል። ነገር ግን ዞን 4 የፋይናንስ ቢሮ ባልታወቀ ምክንያት ከሥራቸው አግዶ ማመልከቻውን እስካቀረቡበት ቀን ድረስ ለዘጠኝ ዓመታት በመንከራተት ላይ እንደሚገኙ እና ጡረታም ሆነ ደሞዝ እያገኙ አለመሆኑን ይገልፃል፡፡

ይህንን ከፍተኛ በደልና ችግር ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል ያመለከቱ ቢሆንም ማመልከቻውን እስካቀረቡበት ቀን ድረስ አንዳችም መፍትሔ እንዳላገኙ የሚያስረዳ ነበር። በመሆኑም መሥሪያ ቤቱን ባገለገሉበት ጊዜ ማግኘት የነበረባቸውን የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ታስበው እንዲከፈላቸው፤ ከመሥሪያ ቤቱ ባልታወቀ ምክንያት ያለአንዳች የፍርድ ቤት ውሳኔ በመባረራቸው በሕጉ መሠረት የሞራል ካሳ እንዲከፈላቸው እና ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ማመልከቻው እስከቀረበበት ዕለት ድረስ ሊከፈላቸው የሚገባው የወር ደመወዝ ታስቦ እንዲከፈለቸው የጽሑፍ ማመልከቻ በማቅረብ ጠየቁ። ሆኖም በዚህ ጊዜም ተገቢውን ምላሽ አላገኙም። ስለዚህ ወደ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም አመሩ።

**የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ምርመራና ውሳኔ**

አቶ ጉራቻ ሰንበቶ ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ላቀረቡት አቤቱታ ሚያዝያ 2 ቀን 2004 ዓ.ም ምላሽ ሰጠ። መዝገቡ ተመርምሮ በተሰጠው ውሳኔ ላይ እንደተብራራው፤ ያሰናበታቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዞን 4 ፋይናንስ ጽሕፈት ቤት ከአራዳ ክፍለ ከተማ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽሕፈት ቤት ወደ ጉለሌ ክፍለ ከተማ የተዘዋወረ መሆኑን እና ለጊዜው ስለአቶ ጉራቻ ቅጥር፣ ስንብት እና ሌሎች ማስረጃዎችን ማግኘት አልተቻለም። አራዳ ክፍለ ከተማም በጊዜው ግለሰቡ በክፍለ ከተማው ተቀጥረው ስለመስራታቸው የሚገልፅ ማስረጃ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ያላገኘ መሆኑን በጽሑፍ አሳውቋል።

የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በመቀጠል ለአዲስ አበባ ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲም አቶ ጉራቻ ሰንበቶ በመስሪያ ቤቱ የጡረታ ዝርዝር ላይ ተመዝግበው ያሉ መሆናቸውን አስመልክቶ ጥያቄ አቅርቧል። ሆኖም የአዲስ አበባ ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ መጋቢት 3 ቀን 2004 ዓ.ም ለሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም አቶ ጉራቻ የጡረታ መለያ ቁጥራቸውን ካላቀረቡ እንደማያውቃቸው ምላሽ ሰጥቷል።

ተቋሙ በመቀጠል ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ኢኮኖሚና ልማት ቢሮ አቶ ጉራቻን በተመለከተ ‹‹ለምን ተሰናበቱ? እንዲሁም ሊከፈላቸው የሚገቡ ክፍያዎች ለምን ተቋረጡ? ›› የሚሉ ጥያቄዎችን አቀረበ። የፋይናንስ ኢኮኖሚና ልማት ቢሮም በሰጠው ምላሽ፤ አቶ ጉራቻ በሞሉት የሕይወት ታሪክ ፎርም መሠረት ጡረታ የሚወጡት ከግንቦት 30 ቀን 1994 ዓ.ም ቀጥሎ መሆኑን አውቀው የጡ-28ን ፎርም እንዲሞሉ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው መደረጉን የተሰጣቸውን ደብዳቤ ፎቶ ኮፒ አያይዞ ያቀረበ መሆኑን እንባ ጠባቂ ተቋም ለአቶ ጉራቻ በሰጠው የጽሑፍ ምላሽ ላይ ተመላክቷል።

በተጨማሪ በመስከረም 14 ቀን 1995 ዓ.ም አቶ ጉራቻ ጡ-28 ፎርም ሞልተው ጡረታቸውን እንዲጠቀሙ ተጠይቀው፤ ሊቀርቡ ፈቃደኛ ያልሆኑ መሆናቸውን በመግለፅ፤ በተጨማሪ ባለ25 ነጥብ የተለያዩ መጠይቆችን የያዘ በክልል 14 መስተዳድር የመንግሥት ሠራተኞች የሕይወት ታሪክ መመዝገቢያ ላይ ሰኔ 6 ቀን 1987 በፊርማቸው አረጋግጠው የሞሉትን ቅፅ በማያያዝ የጡረታ መውጫ ቀኑን በግልፅ በሚያመላክት መልኩ ለሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የሞሉትን ቅፅ ኮፒ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ኢኮኖሚና ልማት ቢሮ ለሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ማቅረቡን አስመልክቶም እንባ ጠባቂ ለአቶ ጉራቻ አስታውቋል።

ሌሎችም በጥቅምት 13 ቀን 1989 የተሰጣቸውን የሥራ ምደባ እና በ1994 ዓ.ም የደመወዝ ማስተካከያ የተደረገላቸው መሆኑን የሚያመላክቱ የተለያዩ ማስረጃዎችን ከፋይላቸው ላይ ኮፒ በማድረግ ማግኘት የቻለ መሆኑን የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም አመልክቷል። የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ምርመራውን ሲያጠቃልል አቶ ጉራቻ ‹‹መብቴን ለማስከበር ተገቢውን ማስረጃ አላገኘሁም›› ለሚለው ጥያቄያቸው ተቋሙ ባደረገው ማጣራት ተጠሪው ተቋም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ መሆኑን አረጋግጧል።

ነገር ግን መስሪያ ቤቱ በደል አድርሶብኛል በሚል ለቀረበው አቤቱታ አንድ ሠራተኛ የጡረታ ዕድሜው ለጡረታ ሲደርስ ጡረታ እንዲወጣ ሠራተኛው እና መስሪያ ቤቱ በጣምራ ኃላፊነታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል። በመሆኑም መስሪያ ቤቱ አቶ ጉራቻ ለጡረታ ዝግጅት እንዲያደርጉ በደብዳቤ ማሳወቁን ከፋይል ላይ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፤ ይህም ተቋሙ ግዴታውን እንደተወጣ ያመለክታል ሲል ገልፆ ውሳኔ አስተላልፏል።

በውሳኔውም አቶ ጉራቻ ማግኘት አልቻልኩም ያሏቸውን ሰነዶች ተቋሙ በማፈላለግ ያገኛቸውን ማስረጃዎች ኮፒ መውሰድ እና ያገለገሉበትን መስሪያ ቤት በመጠየቅ የጡረታ እና ሌሎችንም አለኝ የሚሉትን መብት መጠየቅ ይችላሉ ሲል ገልጿል። በሌላ በኩል ቀጣሪ መስሪያ ቤቱ የጡረታ መውጫ ጊዜውን በደብዳቤ በቅድሚያ ማሳወቁ አስተዳደራዊ በደል አድርሷል ለማለት የማያስችል መሆኑን በማሳወቅ መዝገቡን ዘግቷል።


**የጡረታ ልውጣ ጥያቄ**

አቶ ጉራቻ ወደ ላይ ወደታች ሲሉ እስከ 2005 ዓ.ም ድረስ የጡረታ አበል ሳይከፈላቸው ለ11 ዓመት ቆዩ። በኋላም የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በሰጣቸው ማስረጃ ላይ ተመስርተው ወደ ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ በመሔድ የጡረታ ጥያቄ አቀረቡ። ተቋሙ በበኩሉ አቶ ጉራቻን የተመለከቱ አስፈላጊ መረጃዎች ማለትም ይከፈላቸው የነበረ የደመወዝ ዝርዝር፣ ሲቀጠሩ የሞሉት የሕይወት ታሪክ ፎርም፣ ሥራ ካቋረጡበት ጊዜ ጀምሮ የጡረታ መብታቸውን ያልተቀበሉበት ምክንያት በጽሑፍ እንዲቀርብ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ኢኮኖሚና ልማት ቢሮን ጠየቀ፡፡

በመጨረሻም ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ አቶ ጉራቻ የጡረታ መብታቸው ተፈቅዶ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በየወሩ የጡረታ አበል ማግኘት ጀመሩ። በመቀጠል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ፍረዱኝ



በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮ
ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT FINANCE BUREAU

ቁጥር 16ገ1446/20,746
Ref No.
ቀን 02-9-94
Date

ለአቶ ገበየሁ ወ/ሰንበት ቆርቻ
ዞን 4 ፋ/ጽ/ቤት

ጉዳዩ፦ የጡረታ መውጫ ጊዜዎ በመድረስ ባለተጠቀሙበት የዓመት ፈቃድ እንዲጠቀሙ ስለማሳወቅ፡፡

ፎርም ሚያዚያ 11 ቀን 1968 ዓ.ም. በሞሉት የህይወት ታሪክ
መሠረት የጡረታ መውጫ ጊዜዎ ከግንቦት 30 ቀን 1994ዓ.ም.
ስለሆነ በኃላፊነት የተረከቡትን ንብረት ሁሉ በማያዳግም
ሁኔታ የገቢዎች ዋና ክፍል ለሚመደበው ሠራተኛ በማስረከብ የአለ
ተጠቀሙበትን የዓመት ፈቃድ ጠይቀው ጡ-28 ፎርም አስሞልተው ጡረ
ታዎን እንዲያስጠርሱ እናስታውቃለን፡፡
የገቢዎች ዋና ክፍልም ይህንኑ አውቆ ርክክቡን በአግባቡ
አስፈጽሞ ... እንዲያቀርብ የዚህ ደብዳቤ ቅጂ ተደርጎለታል፡፡

ከሰላምታ ጋር
የፋይናንስ ቁ/ክፍል ተወካይ

ገልባጭ፦
ለበጀት ክፍያ
ለገቢዎች ዋና ክፍል
ለኦዲት አገልግሎት
ዞን 4 ፋ/ጽ/ቤት

5 26 80 FAX/ፋክስ 55 16 85 ✉ 205 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa - Ethiopia
E-mail: aa.cgfb@telecom.net.et

ላለፉት ጊዜያት ማለትም ከ1994 ዓ.ም እስከ 2005 ዓ.ም ያልተከፈላቸው የጡረታ አበል እንዲከፈላቸው ጥያቄ አቀረቡ።

**ያልተከፈለ የጡረታ አበል ጥያቄ**

አቶ ጉራቻ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የጡረታ አበላቸውን በየወሩ መውሰድ ቢጀምሩም ለ11 ዓመታት ሳይከፈላቸው የቆየው ገንዘብ እንዲከፈላቸው ጠየቁ። ይህን ለ11 ዓመታት መከበር ያለበት የጡረታ መብትን ጨምረው ሌሎችም በተመሳሳይ መልኩ በደል ደርሶብኛል ያሉባቸውን ጉዳዮች አካተው በግንቦት 7 ቀን 2010 ዓ.ም ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ማመልከቻ አስገቡ። በመቀጠል ነሐሴ 22 ቀን 2010 ዓ.ም ደግሞ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ ጽሕፈት ቤት ማመልከቻ አቀረቡ። በመጨረሻም በታህሳስ 23 ቀን 2012 ዓ.ም ለኢፌዴሪ የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ለአዲስ አበባ ሪጅን ጽሕፈት ቤት ጥያቄውን አቀረቡ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዞን 4 ፋይናንስ ጽሕፈት ቤት ውስጥ በቋሚ ሠራተኝነት በማገልገል ላይ እያሉ ከመስሪያ ቤቱ አስተዳደር ጋር ባለመግባባታቸው ያለፍላጎታቸው በጡረታ እንዲገለሉ መደረጉን አስታውሰው፤ ሆኖም እስከ 2005 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ምንም ዓይነት ጡረታ ሳያገኙ በችግር የቆዩ በመሆኑ መመሪያው የሚፈቅድላቸውን ሊያገኙ ይገባቸው የነበረው የጡረታ አበል እንዲሰጣቸው ጥያቄ አቅርቡ። ነገር ግን «ከማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲም» ተገቢውን ምላሽ አላገኘሁም በማለት ወደ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል መጡ። የዝግጅት ክፍሉ በቅድሚያ ጉዳዩን ለመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ አዲስ አበባ ሪጅን ጽሕፈት ቤት አምርቷል።

**የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ምላሽ**

የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ አዲስ አበባ ሪጅን ፅሕፈት ቤት የአበል ውሳኔና ክፍያ ባለሞያ አቶ ሰብስቤ ኃይለማርያም እንደሚናገሩት፤ ፋይላቸውን አይተው እንዳረጋገጡት የጡረታ አበል የተወሰነላቸው በመሆኑ በመረጡት ባንክ በየወሩ የጡረታ አበሉ እየተከፈላቸው ነው።

የዝግጅት ክፍሉ «አቶ ጉራቻ በ1994 ዓ.ም ጡረታ የመውጫ ዝግጅት አድርጉ የሚል ደብዳቤ ሲደርሳቸው፤ እርሳቸው ጡረታ መውጫ ዕድሜዬ ገና ነው ብለው ቅሬታ አቅርበው ነበር። እናንተ ጋር ባለው መረጃ መሠረት የጡረታ መውጫ ጊዜያቸው ደርሶ ነበር? » በሚል ላቀረበው ጥያቄ አቶ ሰብስቤ በሰጡት ምላሽ፤ በጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/95ም ሆነ በተሻሻለው በጡረታ አዋጅ ቁጥር 714/2003 መሠረት አንድ ሠራተኛ የመጦሪያ ዕድሜው 60 ዓመት ነው። እርሳቸው ደግሞ መጋቢት 11 ቀን 1959 ዓ.ም ላይ በሞሉት የሕይወት ታሪክ ፎርም መሠረት ጥር 18 ቀን 1936 ዓ.ም መወለዳቸውን ያሳያል። ስለዚህ ጡረታ መውጫ ጊዜያቸው 1996 ዓ.ም ላይ 60 ዓመት ሲሆናቸው ነበር።

ኤጀንሲው እንደሚያውቀው ግን፤ እርሳቸው በፍቃዳቸው ጡረታ የመውጣት ጥያቄ ያቀረቡት 2004 ዓ.ም ነው። ኤጀንሲው ደግሞ በመመሪያ መሠረት ተቀጥረው ለነበሩበት መስሪያ ቤት ከተቀጠሩበት 1957 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም ማገልገላቸውን በቅፅ 2 ፎርም ተሞልቶ እንዲላክ ጠይቋል። ዕድሜያቸው ከሞላ በኋላ ካገለገሉም ከዕድሜ ጣሪያ በላይ የከፈሉት የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ይደረግላቸዋል ብሎ እንደነበር አቶ ሰብስቤ ያስረዳሉ።

ነገር ግን እርሳቸው መብታቸውን እየጠየቁ ስላለው ዓመታት ሲያገለግሉበት የነበረው ተቋም ምላሽ አልሰጠም። አሁንም እዚያ ሲያገለግሉ ከነበረና ከጡረታ መውጫ ዕድሜያቸው በላይ ጡረታ ተቆርጦባቸው ከሆነ ተመላሽ ይደረግላቸዋል ብሏል፡፡

እንደአቶ ሰብስቤ ገለፃ፤ በጥር 20 ቀን 2012 ዓ.ም የ11 ዓመት ጡረታ ታስቦላቸው እንዲከፈላቸው ጥያቄ አቅርበው ቅሬታቸው በኮሚቴ እና በባለሞያ ታይቷል። ስለዚህ የተሰጠው ውሳኔ እስከ 1996 ዓ.ም የነበረው አገልግሎት ተይዞ በወቅቱ 294 የጡረታ አበል ይከፈላቸው ነበር፤ በኋላ ተሻሽሎና ደመወዛቸው ተሰልቶ ጡረታ 1258 ብር ሲያገኙ ነበር። አሁን ደግሞ ከመስከረም ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮ ባለው ማሻሻያ መሠረት 2258 ይከፈላቸዋል።

ኤጀንሲው አቶ ጉራቻን በሚመለከት ደብዳቤ በመፃፍ ሲቀጠሩ የሞሉት ፎርም፤ የደመወዝ ዝርዝር ከመጠየቅ በተጨማሪ ለ11 ዓመታት ጡረታ ያልተቀበሉበትን ምክንያት እንዲገለፅ ሲል ጠይቋል። ማድረግ የሚችለው ይህንን ብቻ ነው። የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የተሰጠው ስልጣን አንድ አሰሪ መስሪያ ቤት በገባው ውል መሠረት በዲሲፕሊንም ሆነ በብቃት ማነስ ወይም በተደጋጋሚ ሥራ ላይ ባለመገኘትና በሌሎችም በልዩ ልዩ ምክንያቶች ሠራተኛውን ጡረታ ውጣ ማለት ይችላል። አቶ ጉራቻ ግን ጡረታ ውጡ ሲባሉ የማያምኑበት ከሆነ ለሰብአዊ መብት ወይም ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ማቅረብ ነበረባቸው። በኤጀንሲው በኩል ግን እርሳቸው ቅሬታውን እንዳቀረቡ ተቋሙን በደብዳቤ ጠይቆላቸው ምላሽ መስጠት የነበረበት ቀጣሪ መስሪያ ቤቱ ምላሽ አልሰጠም።

አቶ ጉራቻ ለመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ጥያቄ አቅርበዋል። ኤጀንሲውም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ ጥያቄ ያቀረበ ሲሆን፤ ያቀረቡት የግለሰቡን መብት ለማስጠበቅ እንደነበር አቶ ሰብስቤ ይናገራሉ፤ በማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ በኩል አንድ ተገልጋይ ቅሬታ ካለው በጽሕፈት ቤቱ በሦስት ኮሚቴ ታይቶ በተሰጠው ውሳኔ ካልረኩ እንደገና ይግባኝ ማለት ይችላል። አቶ ጉራቻም ይግባኝ ብለው በሕጉ መሠረት ታይቶላቸዋል። የቀረባቸውና 11 ዓመት ሙሉ ሊከፈለኝ ይገባል የሚሉትን ማድረግ የሚቻለው አሰሪው መስሪያ ቤት በእነዚህ ጊዜያት እያሠራቸው ከነበረ እና የጡረታ ከተቀነሰ የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይከፍላል። ከዚህ ውጪ አሁንም ካልረኩ እርሳቸው በድጋሚ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ ሲል ምላሽ ሰጥቷል።

ኤጀንሲው ለጡረታ ከደረሱበት ዕድሜ ጀምሮ ያልከፈለውን መክፈል የለበትም? በሚል ላቀረበው ጥያቄ ባለሞያው በሰጡት ምላሽ ላይ እንደገለፁት፤ በአቶ ጉራቻ ፋይል ጥር 18 ቀን በ1936 መወለዳቸው ተሞልቷል። በማህበራዊ ዋስትና ሕግ መሠረት አንድ ሠራተኛ የጡረታው ቀን የሚሰላው በመጀመሪያ በሞላው የሕይወት ታሪክ ነው። ሌላ ቦታ ላይ 1939 ዓ.ም ብለው ሞልተዋል። ሌላም ቀን በሌላ ተቋም የተለየ አድርገው ቢሞሉም የሚያዘው የመጀመሪያው ነው።

ተቋሙ አሰሪው መስሪያ ቤቱ በሚልከው ዝርዝር መሠረት ማለትም ደመወዛቸውን እና የሕይወት ታሪካቸውን ገልፆ የጡረታ አበሉን ይከፍላል፤ እንጂ ይህ ሳይሟላ ጡረታ የሚከፍልበት ሁኔታ የለም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።

በተጨማሪ የዝግጅት ክፍሉ አንድ ሠራተኛ ጡረታ መውጣት እያለበት ጡረታ ካልወጣ ወይም አሰሪ መስሪያ ቤቱ ጡረታ መውጣት እንዳለበት ካላሳወቀ እናንተ ጥያቄ አታቀርቡም? በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ አንድ ሠራተኛ ጡረታ የሚወጣው ዕድሜው ሲደርስ ተቋሙ ጡረታ እንዲወጣ ሲጠይቅ ወይም 55 ዓመት ከሞላው እና 25 ዓመት ካገለገለ ሠራተኛው ራሱ ጥያቄ ካቀረበ አሊያም ከላይ እንደተገለፀው በተለያዩ ምክንያቶች አሰሪ መስሪያ ቤቱ ሠራተኛው ጡረታ እንዲወጣ ጥያቄ ካቀረበ ብቻ ጡረታ እንዲወጣ ፈቅዶ ክፍያውን ይፈፅማል እንጂ ከዚህ ውጪ ሌላ አሠራር የለም ሲሉ ተናግረዋል።

**አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ኢኮኖሚና ልማት ቢሮ**

ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ኢኮኖሚና ልማት ቢሮ አቶ ጉራቻ ሰንበቶ (አቶ ገበየሁ ወ/ሰንበት) በተቋሙ ስለመስራታቸው፤ በሞሉት የሕይወት ታሪክ ፎርም መሠረት ጡረታ የሚወጡት መቼ እንደነበር እና ለምን ከግንቦት 30 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምረው የጡ-28ን ፎርም እንዲሞሉና ለጡረታ ዝግጅት እንዲያደርጉ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው ተደረገ? በማለት ጥያቄ ለማቅረብ አቅደን ቢሯቸው ድረስ ሔደናል።

በተጨማሪ በጊዜው ባለ 25 ነጥብ የተለያዩ መጠይቆችን የያዘ በክልል 14 መስተዳድር የመንግሥት ሠራተኞች የሕይወት ታሪክ መመዝገቢያ ቅፅ የተሞላው እና በፊርማቸው የተረጋገጠው ፎርም ላይ እንደገለፁት፤ የተወለዱት መቼ ነው? የሚል እና የ11 ዓመት የጡረታ አበላቸው ለምን አልተከፈላቸውም? ለዚህ ኃላፊነቱን የሚወስደው ማን ነው? እናንተ በ1994 ዕድሜያቸው ደርሷል ብትሉም የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የአዲስ አበባ ሪጅን ደግሞ ቀድመው በሞሉት የሕይወት ታሪክ መሠረት ዕድሜያቸው የሚደርሰው በ1996 ዓ.ም መሆኑ ከፋይላቸው ጋር ተያይዟል ብሏል። እናንተ ከምትሉት ጋር እንዴት ተለያየ? ስንል ለጥያቄዎቹ ምላሽ እንዲሰጡን አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ኢኮኖሚና ልማት ቢሮ ሁለት ጊዜ በአካል ሔደን ጥያቄ አቅርበናል።

ነገር ግን ምላሽ ማግኘት አልቻልንም። ሆኖም ፋይሉን ፈልገው ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆናቸውን የገለፁ ሲሆን፤ በአቶ ጉራቻ ( በአቶ ገበየሁ) ጉዳይ ላይ ምላሻቸውን ከሰጡን ይዘን የምንቀርብ ይሆናል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## ዓለም አቀፍ ሙሾ አርጋጆችና አስረጋጆች

**የዕድሜ ጧት የትዝታ ወግ፤**

የሕወሓት ነገር ቢወቅጡትም ሆነ ቢሰልቁት እነሆ ግራ እንዳጋባ ዘልቋል። "ነገረኛ ሰው ከቤቱ አይሞትም" ይላሉ አበው - እውነታቸውን ነው። "ነገረኛ ናቸው አጥልቃችሁ ቅበሯቸው፤ የተነሱ እንደሆን ብዙ ነው ጣጣቸው" እየተባለም ይነገራል። ለማንኛውም ወደዋናው ጉዳያችን ከመግባታችን አስቀድሞ ረዥሙ ንባበ መንገዳችን "የውሃ መንገድ" እንዲሆንልን ጉዟችንን በነበር ወግ እናሟሽ።

ድርጊቱ ተፈጸመ የሚባለው ኮልፌ ጅማ ሠፈር አካባቢ ነው። ዘመኑ ደግሞ ከግማሽ ክፍለ ዘመን ላቅ ይላል። ይህንን ክስተት የምታስታውሱ የያኔዎቹ ታዳጊ የዕድሜ እኩዮቼ ወይንም ዕድሜውን ያደላችሁ የወቅቱ የአባባ ባጫ እድር አባላት በቃላችሁ ምሥክርነት እውነታውን ብታኅላምሱት አይከፋም። "ጉድ! ጉድ!" እየተባለ በዘመኑ የተወራለት ታሪክ እነሆ እንደሚከተለው ይታወሳል።

ሴትዮዋ የአካባቢውን ነዋሪዎች በባህርይም ሆነ በግብር እጅግ ያስቸገሩ ነበሩ ይባላል። የተንኮል ተግባራቸው፣ ነበልባል እሳት እየተፋ ለጠብ የሚጋበዙበት አንደበታቸው፣ ፈጠራ እያከሉበት የሚያዛምቱት በሬ ወለደ ወሬያቸው የአካባበውን ነዋሪ ጤና መንሳት ብቻ ሳይሆን ብዙዎችን አቃቅሮ ለከፋ ድርጊትም አዳርሶ ነበር ይባላል። አልፎም ተርፎ ነፍስ ያላወቁ ታዳጊ ሕጻናትንና ልጃገረድ ሴቶችን ወደ አልባሌ ሕይወት እንዲገቡ ያስኮበልሉ ነበርም እየተባለ ይወራል። እኚሁ ሴትዮ እንኳን ለሰፊው ማኅበረሰብ ይቅርና ለራሳቸው ቤተሰቦችም ሳይቀር ፈተና እንደሆኑባቸው በአሉ ተባባሉ የአንደበት ቅብብሎሽ እየተነገረ በስፋት ተወርቷል።

አይቀሬው ሞት ቀጠሮውን ማክበሩ ግድ ነውና እኚህ ሞገደኛ ሴት በጥቂት ቀናት በሽታ አልጋ ላይ ሲያጣጥሩ ሰንብተው ሕይወታቸው ማለፉ ተረጋገጠ። በወጉና በደንቡ መሠረትም ከቤተ ዘመዶቻቸው መካከል አንድ ሰው ወደ "የአባባ ባጫ" የእድር ዳኛ ዘንድ በመሄድ የቀብሩ ሁኔታ እንዲመቻች ሪፖርት አደረገ። መልእክቱን የተቀበሉት የእድሩ ዳኛም እልፈታቸው፣ የቀብሩ ሰዓትና ቦታ ለእድርተኞቹ እንዲለፈፍ ለጡሩንባ ነፊው ትዕዛዝ አስተላለፉ።

ጡሩንባ ነፊውም በተሰጠው የአለቃው ትዕዛዝ መሠረት ወፍ ጭጭ ከማለቱ አስቀድሞ በአካባቢው እየዞረ "የአባባ ባጫ እድርተኛ የሆናችሁ በሙሉ ወ/ሮ...ስላረፉ ለቀብር እንድትወጡ። ቀብሩ የሚፈጸመው አማኑኤል ቤ/ክርስቲያን በስድስት ሰዓት ላይ ነው።" በማለት ልፈፋውን አጧጧፈው።

የሟችቷ ዜና እረፍት በይፋ መገለጡን ያልተስማሙ የቤተሰቡ አባላት ለልፈፋ የወጣውን ጡሩንባ ነፊ እያዋከቡ ወደ እድሩ ዳኛ ዘንድ በመውሰድ በአስቸኳይ ቀብሩ እንደማይፈጸም ማስተባበያ እንዲሰጥ ግብ ግብ ፈጠሩ። ምክንያታቸው ደግሞ ሞታቸውን የአካበቢው ሰው እንዳይሰማ ስለፈለጉ ነው።

በባህርያቸውና በተግባራቸው ጥዩፍነት በቁማቸው ሲታሙና ሲብጠለጠሉ የኖሩት አንሶ ከሞቱ በኋላም ሕዝብ በነቂስ ተሰብስቦ "እንኳን ድብን አሉ! ሞት ሲያንሳቸው ነው" እየተባለ በሙሾና በረገዳ ተሳቦ እንዲታሙና መሳለቂያ እንዲሆኑ ስላልፈለጉ ነበር። ቀብሩን ራሳቸው የቤተሰቦቹ አባላት በጨለማና በድብቅ ወስደው እንደሚቀብሯቸውም ለእድሩ ዳኛ አስረግጠው አስታወቁ። ከዚያ በኋላስ "ምን ተፈጸመ?" የሚለው የታሪኩ መደምደሚያ ለጊዜው በይደር መተላለፉን መርጠናል። ሁኔታው ሲመቻች ታሪኩን እንደመድማለን።

**የሙሾ ነገር ከተነሳ አይቀር፤**

በበርካታ የሀገራችን ባህሎች ውስጥ ለሟች ቀብር ከሚከወኑ የጋራ ልማዶች መካከል አንዱ ሙሾ ነው። ሙሾ በተመረጡ ግጥሞችና ዜማ እየተዋዛ ከቀብር በፊት ለአስከሬን ሽኝት የሚፈጸም የረገዳ ትርዒት ነው። ሟች ሴትም ይሁን ወንድ፣ ወጣትም ይሁን አዛውንት፣ ፈሪም ይሁን ጀግና ብቻ ለሁሉም አፈር ቀማሽ በድን የሚዥጎደጎደው ግጥምና ዜማ በመወድስ የደመቀ ነው።

ሙሾ አውራጇ ወይንም አውራጁ ቀብሩን ለማድመቅ የሚጋበዙት ጠቀም ያለ ክፍያ ተከፍሏቸው ነው። የሟቹን ማንነት ማወቅ ያለማወቅ ግዴታ አይደለም። የሚፈለገው መሠረታዊ የሚባሉትን የሟቹን ዕድሜ፣ ፆታ፣ ቤተሰባዊ አቋምና የሙያውን መረጃ ጠይቆ መረዳት ብቻ ነው። ከሙሾ ረገዳው ስምሪት አስቀድሞ ዋናው ሙሾ አሙሺ የምግብና የመጠጥ መስተንግዶም ይቀርብለታል። ግብዣው የሚፈጸመው ብዙውን ጊዜ ጠንከር ባሉ የአልኮል መጠጦች ታጅቦ ነው። የዚህ ምክንያቱ ሙሾ አስረጋጁ በአልኮሉ ድጋፍ እንዲበረታታና ድካም እንዳይሰማው ለማድረግ ታስቦ ይመስላል።

ከዚያ በኋላማ ምን ይጠየቃል፤ "ባለሙያው ሙሾኛ ካጠራቀማቸው የግጥም ስብስቦቹ መካከል እየመዘዘ "ሆ! ሆ!" በማሰኘት እምባ ማራጨት ነው። እርሱ ወይንም እርሷ ደረታቸውን ለአመል ያህል ነካ ነካ እያደረጉ ግጥሙን ሲያዥጎደጉዱ አንዳንድ ቀብርተኞችና የቤተሰቡ አባላት ደረታቸውን እየደቁ ሀዘናቸውን አምርረው ይገልጻሉ። አንዳንዶችም ምርር ትክን ብለው የሚያለቅሱት የራሳቸው የቀደመ ሀዘን እየታወሳቸው እንደሚሆንም አይካድም።

አልቃሽ አያለቅስም፤ እንዲያለቅስም አይገደደም። የእርሱ ተልዕኮ ሌሎችን ማስለቀስና ማስረገድ ነው። ምንም እንኳን የምር ነው ብለን ባንቀበለውም አንዳንዴ ከቤተሰብ አባላት መካከል አብሬ ካልተቀበርኩ ብለው ለያዥ ለገራዥ የሚያስቸግሩ አይጠፉም። ይህን መሰሉ በትራዥዲ ክስተት ውስጥ የሚስተዋለው የኮሜዲ ትርዒት በብዙ የሀገራችን ክፍሎች ዛሬም ድረስ ሙሉ ለሙሉ ስለመቅረቱ አስረግጦ ለመናገር ያዳግታል።

ለማንኛውም አልቃሽ ያስለቅሳል እንጂ አብሮ እንደማያለቅስ ካስታወስን ዘንድ ወደ ዋናው ጉዳያችን ዘልቀን ሞቶም ቢሆን ቀብሩ እንዲደበቅለት ስለሚፈለገው፤ ሞቱን በተቀበሉ አንዳንዶች ዘንድም "ወደ መቃብር ከመወሰዱ አስቀድሞ ሙሾው እየደመቀለት ስለሚንቆለጳጳሰው አሸባሪው ትህነግ ና አስለቃሾቹ ጥቂት አጠቃላይ ዳሰሳ እናደርጋለን።

የአሸባሪው ትህነግ አልቃሾችና አስለቃሾች፤

አሸባሪው ትህነግ የቀብር ዝግጅት ከሩቅ ዘመኑ የአባባ ባጫ የእድር ታሪክ ጋር የሚቀራረብ ጠረን ያለው ይመስለናል። ሕወሓት እኮ ከበደነ ሰንብቷል። ችግሩ ነፍሱ ፈጥና ያለመውጣቱና ሠልስቱ፣ ሰባቱም ሆነ አርባው በይፋ ያለመገለጡ ብቻ ነው። "ልጡ ተርሶ፤ ቀብሩም ተምሶ" እየተጠበቀ እንዳለ ዓለም ሁሉ ገብቶታል። ሞገደኛው፣ እብሪተኛው፣ ጨካኙ፣ የጦርነት ሱሰኛውና ዘረኛው የትህነግ ቡድን እስትንፋሱ ጭል ጭል ይበል እንጂ የቆመው መቃብሩ አፋፍ ላይ ነው።

እጅግ የሚያስገርመው ነገር የቡድኑ ሞት ሳይሆን ሞቱን ይፋ እንዳይገለጥ በሙሉ ኃይላቸው እየተንፈራገጡ፣ በአደባባይም ጭምር እየተንከባለሉና አብረን ካልተቀበርን እያሉ በምስለ ሬሳ ተመስለው የሚያላዝኑት ቁጥራቸው መብዛቱ ነው። "ቢሞት እንኳን ሞተ አትበሉ" እያሉ ጥብቅና የቆሙት ኃይላት ቁጥርም በቀላሉ የሚገመት አይደለም። "ሞቱን ብንቀብለም እንኳን ኮሽ ሳይልና ጡሩንባ ሳይነፋ በስውር የምንቀብረው እኛ ብቻ ነን!" በማለት በድብቅና በጨለማ ሲዶልቱ ውለው የሚያድሩት ፀረ ኢትዮጵያ እኩያንም ብዛታቸውም ሆነ ዓይነታቸው የትዬለሌ የሚሰኝ ነው። ሞቱ ለዓለም በይፋ እንዳይገለጥ፣ ቀብሩም በአግባቡ እንዳይነገር የሚውጠነጠነው የሴራ ዓይነት "ቀብር ሽሻጊዎቹን" ትዝብት ላይ መጣል ብቻም ሳይሆን ታሪክ ራሱ ፊት እንደሚነሳቸው የገባቸው እስከማይመስል ድረስ ድብብቆሹን ተያይዘውታል።

ዳሩ በደነደነና እብሪት ባሰባው ልብ የእውነት ቃል ተንቀርቅሮ መች በቀላሉ ሊሰርግ ይችላል? እስትንፋሱ ድርግም ሊል አንድ ሐሙስ ለቀረው ሕወሓት ይሉት ጉድ "አልቃሽና አስለቃሽ" በመሆን የረገዳውን ሜዳ የተቆጣጠሩት ዓለም አቀፍ አስረጋጆች ስማቸውና ዓይነታቸው የተለያየ ይምሰል እንጂ የተልእኳቸው አተገባበር ግን አንድና ተመሳሳይ ነው። በጥቅል ማሳያ እናመለካት።

የመጀመሪያዎቹ አልቃሾችና አስለቃሾች የዚህቺው የአህጉራችን ቤተሰብ አባላት የሆኑ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ናቸው። እነርሱን የሚያስለቅሳቸውና ሌሎችንም እንዲያላቅሱ የሚያስገድዳቸው በዋነኛነት የወዳጃቸው የሕወሓት ሞቶ መቀበርና አፈር የመልበስ ጉዳይ አይደለም። አሸባሪውን ቡድን ተገን አድርገውና ከፊት አሰልፈው ሲፈጽሙት የኖሩት ሴራ ተበጣጥሶ አብረው ግባተ መሬታቸው መፈጸሙ እያንገበገባቸው እንጂ። "ምንትስን የሚወጉት በአህያ ተከልሎ ነው" እንዲሉ፤ እንደ ጋሻ ሲገለገሉበት የኖሩት "የአህያ ባል" ከአንበሶች እንደማያድናቸው በሚገባ ስለተረዱ ነው። ተስፋ አድርገው ሲቃዡ የሚያድሩትም መቃብሩን እያስተዋሉ ሳይሆን "ቢሞት እንኳን በትንሣኤ መነሳቱ አይቀርም" ብለው ተስፋ በማድረግ ጭምር ይመስላል።

ሁለተኞቹ ሙሾ አሙሺዎች ማርቲን ፕላውት የሚወክላቸው ስብስቦች ናቸው። አሸባሪው ትህነግ ከሀገር ካዝናና ከሕዝብ ጉሮሮ ሲዘርፍ በከረመው ሀብት የቀጠራቸው እኒህን መሰል ግለሰቦችና "በሰብዓዊ መብቶች አስከባሪነት ስም" እያደናገሩ ያሉ አንዳንድ ዓለም አቀፍ ተቋማትም የሚወድቁት እዚሁ ነጥብ ሥር ነው።

እነዚህ "ቀብር አዘግይዎች" የሚታያቸው አሸባሪው ትህነግ ሲሰፍርላቸው የኖረው ቀለብና ዳረጎት አብሮ መቀበሩ እንጂ የቡድኑ ዘለዓለማዊ ህልፈት "አንጀታቸውን" አላውሶ ርህራሄ ስለገባቸው አይደለም። የብድኑን የቀብር ዜና ለማስተባበል የሚሞክሩትም እንደ ተዝካር ድስት ተጥደው በሚውሉበት ቲዩተር እና ሌሎች ማሕበራዊ ሚዲያዎች ላይ የሀዘን ፍራሽ ጎዝጉዘው የፈጠራ ዜና እየፈበረኩ ነው።

ሦስተኞቹ ሙሾ አስረጋጆች ታዋቂነት ካልሆነ በስተቀር ጎሊና ያልፈጠረባቸው አንዳንድ ዓለም አቀፍ የሚዲያ ተቋማት ናቸው። እነዚህ ተቋማትና የሀሰት ካባ ደርበውላቸው እሶሶ የሚሏቸው ጋዜጠኞቻቸው የበሬ ወለደ ዜና እየተቀባበሉ የሕወሓትን "ድል እንጂ ሞቱን እንዳያውጁ" የታወሩት እውነታው ጠፍቷቸው ሳይሆን ጉርሻው እንደሚከብዳቸው ስለተረዱ ነው። የጎሊናቸውን ግሳጼ በጨው አለቅልቀው "ወተቱን እያጠቆሩ፤ ከሰሉን ሲያነጡ" መመልከት እንግዳ አይደለም። ለሀሰታቸው መሸፈኛ የሚጠቀሙት የሶምሶንን ታሪክ ብጤ ነው። የቅዱስ መጽሐፉ ሶምሶን ሹሩባው ተሸልቶ ያበቃለት ቢመስልም እንደገና ፀጉሩ ሲያቆጠቁጥ ኃይሉ ታድሶ ተገዳዳሪዎቹን በሙሉ እንደሚፈጅ በጨበጡት ማይክራፎን እያስተጋቡ የማደንቆር ስልት እየተጠቀሙ ነው።

የባእዳኑ አስቂኝ ድርጊት እንዳለ ሆኖ እጅግ የሚያሳዝነው "ኢትዮጵያዊ" የሚል ቅጽል ተሸክመው ሀገርና ሕዝብን ሲያዋርዱ የሚውሉት "የእንግዴ ልጆች" ተግባር ነው። እነዚህ "የቤት ውላጅ" የቀብር ጡሩንባ ነፊዎች ዛሬ በርቀት ሆነው የሚያስወነጭፉት የውሸት ቀስት ራሳቸውን ነድፏቸው አንገት ደፍተው እንዲኖሩ እንደሚያስገድዳቸው የገባቸው አይመስልም። "ወያኔም ተቀብሮ ሶልዲውም ያልቅና፤ ያስተዛዝበናል ይሄ ቀን ያልፍና" ብለን የትዝብታችንን አሻራ አትመን ለትውልድ እናስተላልፍላቸዋለን።

አራተኞቹና ዋነኞቹ የአሸባሪው ትህነግ አለንልህ ባዮች "በእኛ ብቻ" የትምክህት ክፉ ደዌ ተለክፈው ለራሳቸው አንቱታን ከሌሎች ዘንድም መወድስ በመራብ የተለከፉ "ታላላቅ ተብዬ" ሀገራት ናቸው። "የፍየሏን ሞት አሳበው፤ የውሽሜ ህልፈት የሚያንገበግባቸው" እነዚህ መንግሥታት የሕወሓት የቀብር ሙሾ ወደ ቀረርቶና ሽለላ እንዲለወጥ ቀን ከሌት በመትጋት "በድኑ አፈር እንዳይለብስ" እየተከላከሉ ያሉት የሚገጥማቸው የነገ ውርደት እየታወሳቸው ነው። ለአደራዳሪነትም፣ ለአስታራቂነትም፣ ለእርዳታውም ሆነ ለሰብዓዊ መብት ሙግቱ "ከእኔ ወዲያ ላሳር" በሚል ክፉ እብሪት የተለከፈችው ፊት መሪዋ የያኒኪዎቹ ሀገር አመሏም ሆነ ተግባሯ እንኳን ለሌላውና ለራሷ ሕዝብም ሳይቀር እንቆቅልሽ እንደሆነ ዘመን መሽቶ ጠብቷል።

ኢትዮጵያ በቀጣናውና በመገኛዋ አህጉር ገንና ከወጣችና እንደ ተገዳዳሪ ከሚያዩአቸው ሌሎች ወዳጅ መንግሥታት ጋር በእኩልነት ወንበር ስባ መቀመጧ እንደማይቀር ሲታወሳቸው ይንገበገባሉ፤ ይንጨረጨራሉ። ስለዚህም የመሰሪ እቅዳቸው ሽል ከትህነግ ጋር አብሮ መቀበሩ እንደማይቀር ስላመኑ በተቻላቸው መጠን ይንፈራገጣሉ። የሕወሓት አይቀሬ ቀብር እንዳይፈጸምም አጥብቀው ይከላከላሉ። ቀብሩ እንኳን ቢፈጸም "በጀግና ቀረርቶ እየተፎከረለትና በጃዝ ፋንፋር እየተዘመረለት እንጂ ዋይ! ዋይ!" እየተባለ እንዳይለቀስ እስከ ማስጠንቀቅ ይደርሳሉ።

ያሻቸውን ይበሉና ያድርጉ እንጂ ትህነግ ሞቷል አፈር መልበሱም ግድ ነው። ኢትዮጵያም በዓለም መድረክ ላይ ከፍ ብላ መታየቷ አይቀርም። ፈረሳቸው አሸባሪው ትህነግ ተቀብሮ ጋጣው ባዶ ሲሆንባቸው ምን ብለው ያወሩና ያስወሩ ይሆን? የከርሞ ሰው ይበለንና ሁሉንም በትዝብት እናስተናግደዋለን። ሰላም ይሁን።

# ህገወጦችን በህጋዊ እርምጃ

**ፍሬሕይወት አወቀ**




በአገሪቱ የመጣውን ለውጥ ተከትሎ በተካሄዱ የሪፎርም ሥራዎች አበረታች ለውጥ እየታየ ይገኛል:: በአንጻሩ በተጠበቀው ልክ ውጤት ያልታየባቸው ዘርፎች ስለመኖራቸውም ይታመናል:: ከዚህ አኳያም የጥቁር ገበያና የዋጋ ንረት ይጠቀሳሉ:: የዋጋ ግሽበትና የጥቁር ገበያን በተመለከተ ችግሩ እየተባባሰ የመጣ በመሆኑ ኢኮኖሚያዊ መፍትሔ ለማምጣት መንግሥት የተለያዩ አማራጮችን መውሰዱን ቀጥሏል::

እየተወሰዱ ካሉ እርምጃዎች መካከልም በቅርቡ ብሔራዊ ባንክ የወሰደው እርምጃ ይጠቀሳል:: እርምጃው በተለይም በጥቁር ገበያው ላይ ያለውን ጤናማ ያልሆነ አካሄድ ለማስተካከልና ገበያውን ለማረጋጋት ያለመ መሆኑን የብሔራዊ ባንክ ገዢ ዶክተር ይናገር ደሴ አስረድተዋል::

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ በተለይም የጥቁር ገበያንና የዋጋ ግሽበትን በተመለከተ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፤ በሥራ ላይ ያለውን የንግድ ስርዓት ማዘመን፤ በፊሲካልና ሞኒተሪ ፖሊሲዎች ላይ ለውጦችን ማድረግ ዘላቂ የሆኑ መፍትሔዎች እንደሆኑ ሁሉ፤ ችግሩን በዘላቂነት ማስቀረት እስኪቻል ድረስ ግን ህገወጥ ሥራ በሚሰሩ አካላት ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃዎችን መውሰድ የግድ ሆኖ ተገኝቷል::

የውጭ ገንዘቦችን በመጠቀም የሀዋላ ሥራ የሚሰሩ ህጋዊ ሰዎች ስለመኖራቸው የጠቀሱት ዶክተር ይናገር፤ እነዚህ ሰዎች ህጋዊ እንደመሆናቸው መሥራት ያለባቸው መሆኑን በማመን ህጋዊ ሆነው በሚሠሩ ሰዎች አማካኝነት አገሪቷ ከሀዋላ ብቻ በየዓመቱ በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር የውጭ ምንዛሬ እንደምታገኝ አስታውቀዋል፤ እነዚህ አካላት ሊበረታቱ እንደሚገባ ገልጸዋል::

ይሁንና በህጋዊነት ስም አንዳንድ ህገወጥ ሥራ የሚሠሩ መኖራቸውን ጠቅሰው፣ እነዚህን አካላት መቆጣጠር አስፈላጊ መሆኑን ነው ዶክተር ይናገር ያስታወቁት:: በተለይም ከባንኮችና ከፋይናንስ ተቋማት ጋር መሥራት ሲጠበቅባቸው የማይሠሩና ከባንኮች ውጭ በግላቸው የሀዋላ ሥራን የሚሰሩ ህገወጦች ስለመኖራቸው ተናግረዋል:: በዚሁ ምክንያትም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንድ ዶላር በጥቁር ገበያ ዋጋው ሲመነዘር የሚጨምርበት መጠን በፍጥነት እያደገ መምጣቱ አዲስ የዕለት ዜና እየሆነ መምጣቱንም ጠቅሰዋል::

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ የዚህ ችግር መሰረታዊ ምክንያት የውጭ ምንዛሪ አቅርቦትና ፍላጎት አለመመጣጠን ቢሆንም፤ መሰረታዊ መፍትሔው በውጭ ምንዛሬ አቅርቦትና በውጭ ምንዛሬ አስተዳደር በኩል መሰራት ያለባቸውን የተለያዩ ሥራዎች መሥራት ነው:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ እስከዚያው ድረስ ግን በመሀሉ ችግሩን እያባባሱ ያሉትን ህገወጦች በመቆጣጠር መፍትሔ ማምጣት ተገቢ ነው :: ይህን መሰረት በማድረግም ማን ምን እንደሚሰራ በዝርዝር በማጥናት በህገወጥ የሀዋላ ሥራ ላይ የተሰማሩ 391 የሚሆኑ ሰዎች የባንክ ሂሳባቸው ገንዘባቸውን ጨምሮ እንዲዘጋ ተደርጓል:: ከዚህ በተጨማሪም የስም ዝርዝራቸውን ለፍትህ ሚኒስቴር በመላክም አስፈላጊው ምርመራ ተደርጎ ህጋዊ እርምጃ የሚወሰድባቸው ይሆናል::

ህገወጥ የሀዋላ ሥራ የሚሠሩ ሰዎች የባንክ ባለሙያዎች ድጋፍ ያላቸውና ትብብር የሚያደርጉ እንደሆነም የጠቀሱት ዶክተር ይናገር፤ ይህን ህገወጥ እንቅስቃሴ ለማስቆም ጥረት ያላደረጉና እያወቁ ቸል ያሉ የባንክ ኃላፊዎችና ሠራተኞችን በማጣራት በየደረጃው እርምጃ የሚወሰድባቸው ይሆናል ብለዋል:: በቀጣይም በየጊዜው የሚኖረውን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሞኒተር በማድረግ በህገወጥ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን በቀላሉ መለየት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ እየተሰራ እንደሆነም አስገንዝበዋል::

የባንኩ ገዥ እንዳሉት ህገወጥነትን ለመከላከል የህብረተሰቡ ተሳትፎ ወሳኝ ነው፤ በህገወጥ መንገድ የሀዋላ ሥራ የሚሰሩ፣ በኮንትሮባንድ የወርቅ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩና የሀሰተኛ የገንዘብ ኖቶችን የሚያትሙ፣ የሚያሰራጩና የሚያዘዋውሩ ሰዎች ከህብረተሰቡ የተሰወሩ አይደሉምና ከህበረተሰቡ ጋር በጋራ በመሆን መከላከል እንዲቻል ባንኩ የተለያዩ አሰራሮችን ዘርግቷል:: በህገወጥ ሥራ የተሰማሩ አካላትን ለሚጠቁሙ ሰዎች ባንኩ ማበረታቻ በመስጠት ወሮታውን ይከፍላል፤ የቁጥጥር ሥራውንም አጠናክሮ ይቀጥላል::

በአሁኑ ወቅት እየተስተዋለ ላለው የጥቁር ገበያ መስፋፋት ምክንያቶቹ ዘርፈ ብዙ እንደሆኑ የጠቀሱት ዶክተር ይናገር፣ አንድ ሁለት ብለን ከምንጠቅሳቸው ምክንያቶች በተጨማሪ በተለያየ ምክንያት መባባሱን ተናግረዋል:: ለአብነትም የዋጋ ግሽበትን ታሳቢ በማድረግ መንግሥት የተለያዩ የምግብ ሸቀጦችን እንደ ስኳር፣ የምግብ ዘይት፣ የህጻናት ወተትና የመሳሰሉት በፍራንኮ ቫሉታ አማካኝነት እንዲገቡ መፈቀዱን አስታውሰው፤ ይህ አሰራርም በራሱ ችግር ያለበትና የጥቁር ገበያውን በማባባስ በኩል ጉልህ ድርሻ እንዳለው ነው ያስረዱት::

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ መንግሥት ፍራንኮቫሉታን ሲፈቅድ የነበረው እሳቤ ዶላር ከውጭ አገር ማግኘት የሚችል ማንም ሰው ዶላሩን ተጠቅሞ የምግብ ሸቀጦቹን ወደ አገር ውስጥ በማምጣት ለገበያ ማቅረብ ቢችል የዋጋ ግሽበቱን ሊያረጋጋው ይችላል ከሚል ግምት የነበረ ቢሆንም፤ እንዲህ አይነት ውሳኔዎች ከችግር የጸዱ ባለመሆናቸው የጥቁር ገበያውን በማባባስ ድርሻ አላቸው:: ይሁንና በፍራንኮቫሉታ አማካኝነት እየተፈጠረ ያለውን ኢኮኖሚያዊ አሻጥር ለመከላከል ነጋዴው የሚጠቀመው ዶላር በውጭ አገር ያለና የራሱ ስለመሆኑ የሚያሳይ የባንክ ስቴትመንት እንዲያቀርብ የማድረግ አሰራርን በመከተል ፍራንኮቫሉታን ያለአግባብ እንዳይጠቀሙና ለታለመለት ዓላማ እንዲውል የማድረግ ሥራ ይሰራል::

ከፍተኛ መጠን ያላቸው ምርቶች ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ መሆኑን ያነሱት ዶክተር ይናገር፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገቡ ገቢ ምርቶች ቁጥር ስፍር የሌላቸውና በዓመት ከ18 ቢሊየን ዶላር በላይ የሚያወጡ ዕቃዎች የሚገቡ እንደሆነም ተናግረዋል:: ይህን ከፍተኛ መጠን ያለውን የውጭ ምንዛሪ የሚጠይቁ ምርቶችን ገበያው እስከፈለገ ድረስ መግባታቸው ክፋት የሌለው መሆኑን ገልጸው፤ አገሪቷ አሁን ካለባት የውጭ ምንዛሬ እጥረት እንዲሁም የአገር ውስጥ ምርቶችን ለማበረታታት ሲባል በአንዳንድ ምርቶች ላይ ማስተካከያ የሚደረግ እንደሆነም አስረድተዋል::

ከጥቁር ገበያና ከዋጋ ግሽበት ጋር ተያይዞ የሚስተዋለውን ችግር ለመቅረፍ መሰረታዊና ዘለቄታዊው መፍትሔ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ መሆኑንም ገልጸው፤ ለዚህም የተጀማመሩ በርካታ አበረታች ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል አስፈላጊ እንደሆነ ነው ያስረዱት:: በተለይም ምርትና ምርታመነትን ማሳደግ ለዋጋ ግሽበት ሁነኛ መፍትሔ መሆኑን ጠቅሰው፣ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦትን የሚያሳድጉ ሥራዎችን አጠናክሮ ከመሥራት ባለፈ የተገኘውንም የውጭ ምንዛሬ በአግባቡ መጠቀም አስፈላጊ ነው ብለዋል::

የውጭ ምንዛሪን በአግባቡ ለመጠቀም መንግሥት እየወሰዳቸው ካሉ የተለያዩ እርምጃዎች መካከል የቅንጦት የሆኑ ቁሳቁሶች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ክልከላ ማድረግ አንዱ ሲሆን፤ በዚህም መሰረት በቅርቡ 38 የሚደርሱ ቁሳቁሶች ወደ አገር ውስጥ ገበያ እንዳይገቡ ሆኗል:: መንግሥት መሰል እርምጃዎችን ሊወስድ እንደሚገባ ቀደም ሲል ጀምረው ሲሞግቱ የነበሩ የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎችም በአሁን ወቅት ብሔራዊ ባንክ እየወሰዳቸው ያሉ እርምጃዎች ተገቢነት ያላቸውና ወቅታዊ እንደሆኑ ያነሳሉ::

አገሪቷ አሁን ካለችበት ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ብሔራዊ ባንክ የወሰዳቸው እና እየወሰዳቸው የሚገኙ እርምጃዎች ተገቢነት ያላቸው መሆናቸውን የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዛፉ እየሱስ ወርቅ ዛፉም ይገልጻሉ:: በብሔራዊ ባንክ በኩል እየተወሰዱ የሚገኙት እርምጃዎች በበጎ የሚታዩ ያሉት አቶ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፣ በመንግሥት በኩል በሕገ ወጥ የገንዘብ ክምችት እና ምንዛሬ ላይ እንዲሁም በፍራንኮቫሉታ ላይ የተወሰዱት እርምጃዎች በበጎ የሚወሰዱ መሆናቸውን ተናግረዋል::

በመንግሥት በኩል የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት፤ ያለምንም የውጭ ምንዛሬ ፍቃድ (ፍራንኮ ቫሉታ) በጉምሩክ በኩል በቀጥታ እንዲገቡ የተፈቀደውን ውሳኔ ያለአግባብ ጥቅም ላይ የሚያውሉ አካላት ተግባራቸው ተገቢ አለመሆኑንም ነው የተናገሩት:: ከዚህ አኳያ ሌሎች ቀዳዳዎች ሊኖሩ ስለሚችሉም መንግሥት በዚህ ረገድ ክትትል እንዲያደርግ ይመክራሉ። እየተባባሰ የመጣውን የዋጋ ግሽበት እና የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት መንግሥት የተለያዩ አማራጮችን ሲጠቀም የተዘረጋውን አማራጭ ምክንያት በማድረግ የሚፈጠሩ ችግሮች መኖራቸውን በመጥቀስ ቁጥጥርና ክትትል አስፈላጊ እንደሆነ አስገንዝበዋል::

መንግሥት እየተባባሰ ለመጣው የኑሮ ውድነት መፍትሔ ለማፈላለግ ከሚያደርገው ጥረት በተጨማሪ ለሰሜኑ ጦርነት መቋጫ ሊበጅለት እንደሚገባና ለሰላም መስፈን ሁሉም የድርሻውን መወጣት እንዳለበትም አስገንዝበዋል::

ኢትዮጵያ የገጠማትን የማክሮ ኢኮኖሚ ፈተናዎች በመረዳት ችግሩን ለማቃለል መንግሥት እየሰራ ያለው ሥራ የሚበረታታ እንደሆነ ጠቅሰው፤ ለመፍትሄው የተጀመሩ ጥረቶች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል ሲሉም ተናግረዋል። በአገሪቱ ለሚስተዋለው የኢኮኖሚ ችግር ኃላፊነቱ የመንግሥት ብቻ አድርጎ መመልከት ትልቅ ስህተት መሆኑንም ነው ያሉት አቶ ዛፉ፤ ድርጅቶች በአንጻራዊ ሰላም ሁኔታ ሥራቸውን እንዲሰሩ ማድረግ እንደሚገባም አስታውቀዋል። የኑሮ ውድነቱ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉና አነስተኛ ገቢ ያላቸውን በከፍተኛ ደረጃ ቢያጠቃም፣ የመንግሥትና የግል ዘርፉ ሰራተኞችንም ስለሚጎዳ ጉዳዩ ለመንግ"ሥት ብቻ ሊተው አይገባም ብለዋል።

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህርና ተመራማሪ ፕሮፌሰር ብርሃኑ አርጂ መንግሥት እየወሰዳቸው ያሉ እርምጃዎች አስፈላጊና ተገቢነት ያላቸው ናቸው ይላሉ:: የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ለመቅረፍ በተለይም የቅንጦት ዕቃዎች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ መደረጉ የውጭ ምንዛሬው ወደ ውጭ እንዳይወጣ ያደርጋል፤ እርምጃው ተገቢነት አለው ሲሉ ይገልጻሉ:: ለዚህም ቅድሚያ መሰረታዊ ፍላጎቶች መሟላት እንዳለባቸውም ይገልጻሉ::

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ከ80 በመቶ በላይ ያለው የማህበረሰብ ክፍል የቅንጦት ዕቃ የሚፈልግ አይደለም:: ስለዚህ እጅግ በጣም እጥረት ያለባቸውና ለህዝቡ እጅጉን አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች አሉ:: ለአብነትም መድሃኒቶች፣ የህክምና መሳሪያዎች፣ በኢንዱስትሪ ውስጥ የሚገኙ ማሽነሪዎችና መሰል ቁሳቁስ የቅድሚያ ቅድሚያ የሚያስፈልጋቸው ናቸው:: ስለዚህ ለእነዚህ ቅድሚያ በመስጠት መገዛት አለባቸው::

መንግሥት አሁን ከወሰዳቸው እርምጃዎች በተጨማሪም መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች እንዳሉም ፕሮፌሰር ብርሃኑ ይጠቁማሉ:: ለዶላር እጥረት ምክንያት ከሆኑት መካከል አንደኛው ሙስናና ብልሹ አሠራር መሆኑን ገልጸው፤ ለአብነትም አገሪቷ ወደ ውጭ ገበያ በምትልካቸው ምርቶች የምታገኘውን የውጭ ምንዛሬ በሙስናና በማጭበርበር እዛው በውጭ አገር ባንኮች እንዲቀመጡ በማድረግ አገሪቷ ማግኘት የሚገባትን ገቢ እንዳታገኝ ይደረጋል ሲሉም ነው የጠቆሙት::

ይህም ስልጣንን መከታ በማድረግ የሚፈጠር ችግር መሆኑን ጠቅሰው፣ ባለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ሲተገበር እንደነበና ከ30 ቢሊዮን ዶላር በላይ እዛው መቅረቱን አስታውሰዋል:: መሰል ችግሮች እንዳይፈጠሩ መንግሥት አሁን እየወሰደ ካለው እርምጃ በተጨማሪ ኤክስፖርት የሚያደርጉ ነጋዴዎች ዶላሩን ወደ አገር ውስጥ ይዘው መመለሳቸውንም መቆጣጠር እንዳለበት አስገነዝበዋል:: ከዚሁ ጎን ለጎን ወደ ውጭ ገበያ የሚላኩ ምርቶችን በማሳደግ እንዲሁም ተኪ ምርቶችን በማምረት የውጭ ምንዛሬ እጥረቱን በዘላቂነት መፍታት ይቻላል ብለዋል::

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ምክንያት የለሾችን ቸል እንበል!

**ተገኝ ብሩ**

የአራዳ ቋንቋ የሚጠቀሙ ወጣቶች አብዝተው "ኧረ ላሽ ላሽ" ሲሉ ይሰማል።ያልተመቻቸው አልያም ሲነገር ያልወደዱትን ጉዳይ ይቅርብኝ ለማለት ሲፈልጉ የሚጠቀሙት ነው።እኔም በመንገዴ ላይ በገጠመኝ ጉዳይ "ኧረ ላሽ" ማለት አማረኝ፡፡

ትክክለኛ ባልሆነ ጉዳይ ላይ አቋም ይዘን ስንሞግት፤ በተሳሳተ መንገድ እየተጓዝን "የእኔ ነው ፍፁም ልክ፤ ያንተ ወይም ያንቺ ግን ፍፁም ስህተት ነው" ማለታችን አልበዛም? የእኔ ነኝ ልክ ፍፁም አባዜያችን የሚላቀቀን መቼ ይሆን! በዚህ መንገድ የሚጓዝ ስንቱን ታዘብነው? እኛስ በመንገዱ ተመላልሰን በስንቱ ትዝብት ውስጥ ወድቀን ይሆን?

እውነታውን አብጠርጥራችሁ የምታውቁትን ነገር፣ ግን ይህ እውነት አልያም ትክክል የሆነ ጉዳይ በሌሎች ስለ ጉዳዩ በማያውቁ አልያም የጉዳዩን እውነታ በቅጡ ባልተረዱ ሰዎች በተሳሳተ መልኩ ሲገለፅ ገጥሟችሁ ያውቃል? "እንዴታ በደንብ እንጂ!" ትሉኝ ይሆናል።ምክንያቱም ዛሬ ላይ የምንታዘበው ጉዳይ በዝቷል።አላፊ አግዳሚው ከትክክለኝነት ይልቅ መሳሳቱ በበዛበት ዛሬ ላይ ቆመን ይህ አዲስ ሊሆንብን አይችልም።ሰው እንዴት እውነት ያልሆነን ነገር እውነት ነው ብሎ ተከራክሮ ለማሳመን ይሚገታል?

እውቀታችን ውስን፣ የምናካልለውም በጣም ጥቂቱን ቦታ ሆኖ ሳለ ሁሉን አዋቂ ነኝ ብሎ መጀነን በእውነቱ ለትዝብት ይዳርጋል።ሰው ሁሉን ሊያውቅና ሁሉም ነገር ላይ እውቀት ሊኖረው ፈፅሞ አይችልም።አንተ በሰዎች ጤና ጉዳይ ላይ እስፔሻሊስት ብትሆን እቤትህ ያለ ቧንቧ ቢፈነዳ አልያም ቢበላሽ ቧንቧ ሰሪው ጋር ለመደወል ስልክህን ማውጣትህ አይቀርም፡፡

አንቺ የጠራ የሂሳብ እውቀት ቢኖርሽ አንድ ቀን በስራሽ የሆነ እንከን ተፈጥሮ የሚያስጠይቅሽ ጉዳይ ቢፈጠር የህግ እውቀት ያለው ሰው ማማከርሽ አይቀርም።እናም አንዱ ጋር ያለው ሌላው ጋር ይጎላል፤ ሌላኛው ጋር የጎደለው ደግሞ አንተ ወይም አንቺ ጋር ተሟልቶ ይገኛል።ስለዚህም ምሉዑነት ያለው ሰው ፈፅሞ ሊኖር አይችልም፡፡

ጉዳዮችን ሁሉ የምንረዳበት አልያም የምናይበት መንገድ ሁሌም ጥሩ ሊሆን አይችልም። አብዛኛውን ጊዜ እኛ እውነት የሚመስለንና፤ ሀቅ ነው ብለን የምንከራከርበት ጉዳይ በትክክለኛ ቁመናው ትክክል ላይሆን ይችላል።ታዲያ እኛ እውነት ነው ብለን በጉዳዩ ላይ ማመናችን ሳይሆን ስህተቱ፤ ያንን የተሳሳትንበትን ጉዳይ ትክክለኝነቱ መለየት አለመቻላችን አልያም ደግሞ ትክክለኛ ማስረጃ ላይ ተመርኩዘን አለመቀበላችን ነው።

ከዚህ በላይ ስህተት ደግሞ በእኛ አተያይ ትክክል ነው ወይም አይደለም ያልነው ጉዳይ ላይ በይነን ሽንጣችን ገትረን "በፍፁም! ይሄ ነው እውነትና ትክክለኛው መንገድ" ብለን ለሌሎች ለማስረዳት መሞከራችን ነው።እንዴት እርግጠኛ ያልሆንበት ጉዳይ ለሌሎች ለማብራራትና ለመግለፅ ተዳፈርን?

በዚሁ ሳምንት የገጠመኝና ለዚሁ መነሻ ሀሳቤ ማሳያ የሚሆነኝን አንድ ትዝብቴን ላንሳ።ከስራ መልስ ወደቤት እየሄድኩኝ ነው፤ ጉዞዬ ደግሞ የፐብሊክ ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ባዘጋጀው የመንግስት ሰራተኞችን ጠዋትና ማታ በሚያመላልሰው ሰርቪስ ውስጥ።በራሴ ጉዳይ ጭልጥ ብዬ በሀሳብ ከሄድኩበት አንድ ከፍ ያለ ድምፅ ወደነበርኩበት መለሰኝ።ከተቀመጥኩበት ወንበር ፊት ለፊት ባለ መቀመጫ ላይ ድምጿን ከፍ አድርጋ የምታወራ ወጣት ሴት ንግግር ባይፈልጉም ትኩረትን ይስባል፡፡

በእርግጥ የልጅቷ ጮክ ብሎ ማውራት እዚያ ሰርቪስ ውስጥ የተለመደ ነው።ነገር ግን ልጅቷ አብዛኛውን ጊዜ የምታነሳቸውና የምትሰጣቸው አስተያየቶች የተቃኑ አይደሉም ብዬ ወደመደምደም ስለደረስኩ አብዝቼ አልሰማትም።መጀመሪያ አካባቢ ሀሳቦቿ ሁሉ የምታየውን ነገር ሁሉ ትችት ስታበዛ ትክክል ብትሆንስ ብዬ በእሷ መንገድ ለማየትም የሞከርኩበት ጊዜም ነበር።ነገር ግን ትክክል ያልሆነ ትክክለኛ ነኝ ባይ መሆኗን ስረዳ ተውኩት።

አንዳንዴ ልጅቷ የምታነሳው ሀሳብ ተገቢ አለመሆኑንና ምክንያታዊ ትሆን ዘንድ ልሞግታት እፈልግና መልሼ እተወዋለሁ።ምን አልባት ሰው ያነሳው ሀሳብ ትክክልም ባይሆን ሲቃወሙት አይወድም አይደል! እኔም ሀሳቧን በመቃረኔ ቅሬታ እንዳይፈጠርባት ሰግቼ ዝም ብዬ ደጋግሜ አልፌያታለሁ፡፡

ዛሬ ግን ማለፍ ከበደኝ።ሁለት የተለያዩ ጉዳዮች አንስታ ተችታና አጣጥላ አልፋ ሶስተኛውን ስትጀምር በሶስተኛው ጉዳይ ላይ የራሴን ሀሳብ ለመሰንዘር ተዘጋጀሁ።ልጅቱ እያነሳች የነበረውና እየተቸችው የነበረው የዘንድሮ 12 ክፍል ተፈታኞች የአፈታተን ሁኔታ ላይ ነበር።ትለዋለች፤ እኛም እንሰማለን።ተማሪዎቹን ሆን ብለው ለመጣል አስበው ነው፤ እንዴት ከተማረበት ትምህርት ቤት ተነጥሎ፣ ስልክ እንዳይጠቀም ተከልክሎና ከፍተኛ ቁጥጥር ተደርጎበት ይፈተናል ተማሪው? ከስር ጀምሮ አይቆጣጠሩም ነበር? አሁን ከዚህ ፈተና ወድቆ የት እንዲደርስ ነው፤ አጨናንቀው የሚፈትኗቸው.... ትላለች።

ልጅቷ ቀጥላለች፤ ምንም ተቀባይነት የሌለው የፈተና ስርዓት ነው።የምታወራው ድምፅዋን ከፍ አድርጋና ሀሳቧንም ድምድም አድርጋ ነው የምታወራው።ተማሪውን ማጨናነቃቸው ልክ አይደለም በሚል ልክ ያልሆነ ምልከታዋን አከታትላ ትገልፃለች።በተለይ አጠገቧ የተቀመጠ ወጣት «አዎ! አዎ» እያለ ማገዙ ደግሞ እኔ ሀሳብ እንድሰጥ ገፋፉኝ፡፡

እኔም ሀሳቤን መስጠት ጀመርኩ። ነገር በምሳሌ ቢሆን ይገባልና አንድ ምሳሌ አንስቼ ማውራት ጀመርኩ።እህት ሁለት ታናናሽ ወንድሞች ይኑሩሽና እነዚህ ታናናሽ ወንድሞችሽ የዘንድሮ ተፈታኝ ነበሩ እንበል።አይበለውና እናትሽ ደግሞ ቤት ታመው ከተኙ አመታት አልፏቸዋል።ወንድሞችሽ ተምረው ሐኪም ሆነው እናትሽን እንዲያክሙልሽ ፈለግሽ እንበል፤ ነገር ግን አንዱ ጎበዝ ሌላኛው ደግሞ ሰነፍ ነው። እንደ አጋጣሚ ሁለቱም የ12ኛ ክፍል ተፈታኞች ናቸው ።የትኛው እንዲያልፍና ትምህርቱን በጥሩ ውጤት ተከታትሎ ጨርሶ እናትሽ እንዲያክማቸው ትፈልጊያለሽ? ብዬ ጠየኳት።መልስዋ ቀላል ነበር። "እንዴ ጎበዙ ነዋ ምን ይጠየቃል" ነበር፡፡

አየሽ እህቴ! አሁን ኢትዮጵያም እያደረገች ያለችው መሰል የሆነ በትክክልና በተገቢው መንገድ የሚጓዝ የነገ በሽታዋንም በጠራ እውቀትና ትክክለኛ ውሳኔ የሚያክማትን በመለየት ላይ ናት።አንቺ ጋር ጥሩ እንዲያድግ ፈልገሽ ወደ አገር ሲሰፋና አገር መልካም የሆነ እርምጃ ስትወስድ ስለምን ቅር ትሰኛለሽ፤ ተማሪዎቹ በትክክል ተለይተውና በተጣራ መልኩ ቢያልፉ አገር ከመጠቀሟ ውጪ ምን ይፈጠራል! ብየ ጥያቄም አስተያየትም ሰነዘርኩ።

ልጅቷ ሙግቷን አላቋረጠችም።ደጋግማ የምትለው አይ ልክ አይደለም የሚለውን ቃል ነው።ብዙ አወራን፤ ነገር ግን እኔ መውረጃዬ ደርሶ ነበርና ከዚያ በላይ ቀጥዬ ላሳምናት አልቻልኩም።በእርግጥ ልጅቷም ልክ አይደለም እንጂ ልክ ነው፤ የምትለው አንዲትም ጉዳይ ያለ አልመስል እስኪል ድረስ ተቺ ናት።

አንዳንዴ በየመንገዱ የምንታዘባቸውን ጉዳዮች በተለያየ መነፅር እንመለከታቸው ይሆናል።ነገር ግን እውነት ላይ ያልተመሰረተና መሰረተ ቢስ የሆነ ምክንያት ይዞ እኔ ልክ ነኝ ማለት ያስተዛዝባል።ተጨባጭ ያልሆነ መረጃ ወደ እውነት የማያቀርብ ምክንያት ማቅረብ ግን ደስ አይልም፡፡እንዲህ አይነቱን ነው "ላሽ ላሽ" ማለት የሚገባው።

# ዓለም አቀፍ

## የሩሲያው የስለላ ኃላፊ ስለኒውክሌር ውጥረቱ ምዕራባውያንን ተጠያቂ አደረጉ

የምዕራባውያን አገራት መሪዎች ፕሬዚዳንት ፑቲንን ጨምሮ የሩሲያ ባለስልጣናት የኒውክሌር ሃይላቸውን በዩክሬን ያሰልፉሉ የሚለው ስጋታቸው በተለይም የሩሲያና ዩክሬን ግጭት ከተቀሰቀሰ ወዲህ ጨምሯል።

ነገር ግን የሩሲያው የመረጃ መስሪያ ቤት ኃላፊ ሰርጌ ናሪይሽኪን ይህንን የኒውክሌር ትርክት አስተባብለዋል፤ ምንም እንኳን በከፍተኛ ሁኔታ እየተስተዋለ መሆኑ ቢገለጸም።ናሪይሽኪን ይልቁንም ጣታቸውን ወደ ምዕራባውያኑ አገራት ጠቁመዋል። አገራቸው ሩሲያ በዚህ ግጭት የኒውክሌር ሃይሏን እንደማትጠቀም በድፍረት መናገር ይችሉ እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄም "በርግጥም ምዕራባውያን በሚያራምዱት የኒውክሌር ጦር መሳሪያ ጥቅም ላይ መዋል ትርክት ስጋት አለን" ሲሉ መልሰዋል።

"ሰሞኑን የሩሲያ የመከላከያ ሚኒስትር ከቱርክ፣ አሜሪካ እና ፈረንሳይ አጋሮቹ ጋር በስልክ ተወያይቷል። ዩክሬን ለመጠቀም ስላሰበችው 'ቆሻሻ የኒውክሌር ቦምብ' ነግሯቸዋል" ብለዋል። ባሳለፍነው ሳምንት ዕሁድ ዩናይትድ ኪንግደም፣ አሜሪካ እና ፈረንሳይ በጋራ የሩሲያ መንግሥትን ሃሳብ ተከትሎ መግለጫ ሰጥተው ነበር። 'ግልጽ የሃሰት መረጃ' ሲሉ የጠቀሱትን የሩሲያ መግለጫ አጣጥለዋል።"መላው አለም ይህንን ሙከራ ጦርነቱን ለማጋጋል ምክንያት በመፈለግ የተደረገ መሆኑን ይረዳል" ሲሉም አውግዘውታል።

የሩሲያ የመከላከያ ሙዚየም ውስጥ በተመረቀ አውደ ርዕይ ላይ በተገኙበት ወቅት የስለላ ቢሮ ኃላፊው ከቢቢሲ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ የሰጡት። የኩባን የሚሳይል ቀውስ 60ኛ ዓመት በማሰብ ነበር አውደ ርዕዩ የተካሄደው። የኩባ ቀውስ በመባል የሚታወቀው ይህ ክስተት የሶቪየት ሕብረት ከአሜሪካ ጋር ለ 35 ቀናት ፍጥጫ ውስጥ የገቡበት ክስተት ነበር።

ታዲያ በአውደ ርዕዩ ላይ የቀድሞው የሶቪየት ሕብረት መሪ ኒኪታ ክሩስቼቭ እና የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆን ኦፍ ኬኔዲ ምስሎች በግድግዳው ላይ ተሰቅለው ይታያሉ። ሞስኮ በወቅቱ ወደ አጋሯ ኩባ የላከቻቸው እና ኬኔዲ እንድታስወጣው ጫና ስታደርግባቸው የቆየቻቸውን ሚሳይሎች ምስሎችም በግድግዳው ላይ ተሰቅለው ይታሉ።

ሩሲያ ከኩባው ቀውስ ምን ትማራለች ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ናሪይሽኪን ምላሽ ሰጥዋል።"የኩባ የሚሳይል ቀውስ የሚያስተምረን ነገር ቢኖር መሪዎች በሰጥቶ መቀበል ላይ የተመሰረተ አለማቀፍ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ውስጣዊ ጥንካሬን ማዳበር እንዳለባቸው ነው" ሲሉ መልሰዋል።

በኩባው ቀውስ ወቅት ከረጅም ፍጥጫ በኋላ



የሶቪየቱ መሪም ሆኑ የአሜሪካው ኬኔዲ በሰጥቶ መቀበል መርህ ከፍተኛ ቀውስን ማስቀረት ያስቻለ ውሳኔ ላይ ደርሰው ነበር። ሶቪየት ከኩባ አሜሪካ ደግሞ ከቱርክ ሚሳይሎቻቸውን አንስተዋል። ነገር ግን ከስድስት አስርት ዓመታት በኋላም የሩሲያው መሪ ቭላድ ሜር ፑቲን ለሰጥቶ መቀበል ዝግጁ መሆናቸውን የሚያሳይ ምልክት የለም። አሁንም ቢሆን የኒውክሌር ጦርነት ይኖር ይሆን ወይ? የሚሉ ስጋቶች እንዳንዣበቡ ነው። የዩክሬኑ ጦርነት ከኩባው የሚሳይል ቀውስ በተለይ መቀጠሉን የዘገበው ቢቢሲ ነው።

## እስራኤል በሶሪያ ዋና ከተማ ደማስቆ ዙሪያ ያነጣጠረ ጥቃት ማድረሷ ተገለጸ

የእስራኤል ሚሳይሎች በሶሪያ ዋና ከተማ ደማስቆ አቅራቢያ በሚገኙት ኢላማዎች ያልተለመደ ጥቃት ማድረሳቸው ተገለጸ።እስራኤል በሶሪያ ውስጥ በኢራን እና በኢራቅ የሚደገፉ ሀይሎች የሚንቀሳቀሱበት ናቸው ያለቻቸውን ኢላማዎች ላይ ለዓመታት ጥቃት ስታደርስ ቆይታለች።

ሮይተርስ የሶሪያን ወታደራዊ ምንጭ ጠቅሶ እንደዘገበው በደማስቆ ሱሪያ ብዛት ያላቸው ሚሳይሎች የየተኮሱ ሲሆን የሶሪያ አየር መከላከያ የተወሰኑትን ማክሸፍ ችሏል።"በጥቃቱ ወታደር



ቆስሏል፤ አንዳንድ ቁሳዊ ጉዳት አድርሷል" ሲል ምንጩን ጠቅሶ ዘገባው ገልጿል፡፡

የእስራኤል ጦር አስተያየት ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆነም ብሏል ሮይተርስ።የእስራኤል ጥቃቶች ብዙውን ጊዜ የሚከናወኑት በጨለማ ሽፋን ስር ነው። ኢራን የአየር ማስተላለፊያ መስመሮችን በመጠቀም ሂዝቦላህን ጨምሮ በሶሪያ እና በሊባኖስ ውስጥ ላሉ አጋሮች የጦር መሳሪያ ለማድረስ የምታደርገውን ጥረት ለመግታት እስራኤል በሶሪያ አየር ማረፊያዎች ላይ ጥቃቷን አጠናክራለች፡፡

ቴህራን በመሬት ዝውውሮች ላይ መስተጓጎል ተከትሎ ወታደራዊ መሳሪያዎችን ለጦር ኃይሏ እና አጋር ተዋጊዎች በሶሪያ ለማጓጓዝ በአየር ማድረስን የበለጠ አስተማማኝ መንገድ አድርጋለች ሲል የዘገበው አል ዐይን ነው።

# ስፖርት

## የሴካፋ ከ20 ዓመት በታች ውድድር ዓርብ ይጀመራል

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን ለሴካፋ ዞን ውድድር ወደ ሱዳን ያቀናል። ባለፉት በርካታ ቀናት በአዲስ አበባ የካፍ አካዳሚ ዝግጅቱን ሲያደርግ የቆየው የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን በቅርቡ በተሾሙት አሰልጣኝ እድሉ ደረጄ እየተመራ ከቀናት በፊት ከመቻል የ20 ዓመት በታች ቡድን ጋር የአቋም መፈተሻ ጨዋታ አከናውኖ 3-0 አሸንፏል።

በሱዳን አስተናጋጅነት የሚካሄደው የሴካፋ ዞን ከ20 ዓመት በታች የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ውድድር ጥቅምት 18 የሚጀምር ሲሆን ኢትዮጵያ በምድብ ሁለት ከታንዛንያ እና ዩጋንዳ ጋር መደልደሏ የሚታወስ ነው። ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የምድብ ጨዋታም በመጪው ረቡእ ከታንዛኒያ ጋር እንደምታደርግ ከውድድሩ መርሃግብር ለመረዳት ተችሏል።

ለኢትዮጵያ እግር ካስ ፌዴሬሽን ዩቲዩብ አስተያየታቸውን የሰጡት አሰልጣኝ እድሉ፣ እሳቸውና ምክትሎቻቸው ቡድኑን ለማሰልጠን ሲመጡ የአጭር ጊዜ ኮንትራት ቢፈራረሙም በቅርብ የሚጠብቃቸው የሴካፋ ውድድርን ጨምሮ ወደ ፊት በሚያስመዘግቡት ውጤት መሰረት ረጅም ውል ሊሰጣቸው እንደሚችል በቃል ደረጃ መስማማታቸውን ገልፀዋል፡፡ ለሴካፋው ውድድር ዝግጅት ሲጀምሩም በይፋ ጥሪ ካቀረቡላቸው አርባ ስምንት ተጫዋቾች በተጨማሪ ክፍተት ያለባቸው ቦታዎች ላይ ከየክለቦች ሌሎች ተጫዋቾችን እንዳመጡ ተናግረዋል፡፡

ለብሔራዊ ቡድኑ ከተጠሩት አብዛኞቹ ተጫዋቾች በባቱ፣ጎንደርና አሰላ ከተሞች በተካሄዱ ውድድሮች ላይ የታዩ መሆናቸውን የጠቆሙት አሰልጣኙ፣ ተጫዋቾቹ በልምምድ ላይ የቆዩ በመሆናቸው አሁን እያደረጉ የሚገኙት ዝግጅት በቅርብ ካለው ውድድር ጋር የተያያዘ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በሴካፋ ውድድር ቡድኑ የት ድረስ እንደሚጓዝ ለመናገር በቅድሚያ የተጋጣሚ ቡድኖች ያሉበትን ወቅታዊ



**የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን ለሴካፋ ውድድር በካፍ አካዳሚ ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቷል፣**

አቀም ማወቅ እንደሚጠይቅ የተናገሩት አሰልጣኝ እድሉ፣ በእንዲህ አይነት ውድድሮች ሁሉም ቡድኖች ከስር ጀምሮ ተሰርቶባቸው በቂ ዝግጅት አድርገው እንደሚመጡ አስረድተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድንም ባለው አቅም መሰረት በሚጠቅመው አጨዋወት መሰረት ትኩረት አድርጎ በመዘጋጀት ከሱዳን ጥሩ ውጤት ይዞ ይመጣል ብለው ተስፋ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡

ሰባት ቡድኖች በሚሳተፉበት የዘንድሮው ከ20 አመት በታች የሴካፋ ውድድር ለፍጻሜ የሚቀርቡ ሁለት ቡድኖች በ2023 የአፍሪካ ከ20 አመት በታች አፍሪካ ዋንጫ ላይ በቀጥታ ይሳተፋሉ።

የሴካፋ ከ20 አመት በታች ውድድር በመካከለኛውና ምስራቅ አፍሪካ እግር ኳስ ምክር ቤት አማካኝነት ሃያ አባል አገራትን ያካተተ አንጋፋ የውድድር መድረክ ሆኖ እኤአ ከ1971 ጀምሮ እየተካሄደ ይገኛል።

ውድድሩ ብዙ ጊዜ በየሁለት አመቱ አልፎ አልፎም በሶስትና አራት አመት ልዩነት ሲካሄድ ቆይቷል። ኢትዮጵያም ከዚህ ቀደም ከተካሄዱ አስራ ሁለት ውድድሮች በሶስቱ ዋንጫ ማንሳት ችላለች። ይህም እኤአ በ1995 ኬንያ ባስተናገደችው ውድድር በፍጻሜ ጨዋታ ታንዛኒያን በመርታት ለመጀመሪያ ጊዜ ቻምፒዮን የሆነችበት አንዱ ነው። በቀጣይም ኢትዮጵያ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ባስተናገደችው ብቸኛ ውድድር እኤአ በ1996 ዩጋንዳን በፍጻሜ ጨዋታ አሸንፋ ያነሳችው ዋንጫ ተጠቃሽ ሲሆን፣ እኤአ 2005 ላይ ዛንዚባር ባስተናገደችው ውድድር ቡሩንዲን በፍጻሜ ጨዋታ አሸንፋ ቻምፒዮን እንደነበረች ይታወቃል።

ኢትዮጵያ በዚህ ውድድር ሶስት ጊዜ ቻምፒዮን በመሆን ስኬታማ ከሚባሉ አገራት አንዷ ስትሆን ዩጋንዳ አራት ጊዜ የዋንጫ ባለቤት በመሆን ቀዳሚ ናት። ሁለቱ አገራት (ኢትዮጵያና ዩጋንዳ) ዘንድሮ ሱዳን በኦምዱርማን አል ሂላል ስቴድየም አስራ ሶስተኛውን ውድድር ስታዘጋጅ በአንድ ምድብ ተደልድለዋል። በሁለተኛው የምድብ ጨዋታቸውም በቀጣዩ ሳምንት የሚገናኙ ይሆናል።

በምድብ አንድ አስተናጋጇ ሱዳን ከቡሩንዲ፣ደቡብ ሱዳንና ጅቡቲ ጋር ተደልድለዋል። ውድድሩ በመጪው አርብ ሲጀመርም ሱዳን በመክፈቻው ጨዋታ ጎረቤቷ ደቡብ ሱዳንን ትገጥማለች።


## በድጋሚ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ የግዥው መለያ ቁጥር አአከመባ/ግብዓት/ቡ-1/004-3/2015

የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን በ2015 በጀት አመት ለመንገድ ግንባታ አገልግሎት የሚውሉ ከታች የተገለፁትን የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች በሰዓት የኪራይ አገልግሎት በብሄራዊ ግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛ ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | በሰዓት ለኪራይ የተፈለገ የማሽነሪ ዓይነት | የስሪት ዘመን እ.ኤ.አ (GC) | ብዛት በቁጥር | አጠቃላይ ለኪራይ የሚፈለገው ሰዓት | የጨረታ መለያ ቁጥር | ጨረታ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ | የጨረታ መዝጊያ ቀንና ሰዓት | የጨረታ መክፈቻ ቀንና ሰዓት | የጨረታ ማስከበሪያ በብር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Dozer (≥300 Hp) | ≥ 2012 GC | 3 | እስከ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም | አአከመባ/ግብዓት/ቡ-1/004-3/2015 | 60 ቀን | ጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ከሰዓት 8:00 ሰዓት | ጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ከሰዓት 8:15 ሰዓት | ለአንድ ማሽነሪ 10,000.00 /አስር ሺህ ብር/ |
| 2 | Motor Grader (≥140 Hp) | ≥ 2012 GC | 2 | | | | | | |
| 3 | Chain Excavator (≥1.6m³ heaped and 200Hp) (Bucket) | ≥ 2012 GC | 12 | | | | | | |
| 4 | Chain Excavator (Jack Hammer) ≥200 Hp, for jack hammer min. operating weight shall to be≥2500 kg and min. impact rate shall to be ≥ 350 bpm | ≥ 2012 GC | 2 | | | | | | |
| 5 | Wheel Loader ≥ 3m³ Bucket capacity and ≥ 180Hp) | ≥ 2012 GC | 5 | | | | | | |
| 6 | Wheel Excavator ≥ 1M³ Bucket capacity and 135 HP | ≥ 2005 GC | 6 | | | | | | |
| 7 | Double Drum Roller (4 ton) | ≥ 2008 GC | 5 | | | | | | |
| 8 | Double Drum Roller (7-10 ton) | ≥ 2008 GC | 2 | | | | | | |
| 9 | Pneumatic Roller (≥12 ton (Unballasted) | ≥ 2003 GC | 7 | | | | | | |
| 10 | Backhoe Loader Loader (≥ 1M³ front Bucket capacity, ≥ 0.5 M³ Backhoe bucket capacity, ≥90 Hp) | ≥2005 GC | 2 | | | | | | |
| 11 | Asphalt Paver (paving width ≥2.5m without screed, Engine capacity ≥150 hp, wheeled/chain drive) | ≥ 2005 GC | 3 | | | | | | |
| 12 | Water trucks ≥13,000Lit. | ≥2010 GC | 2 | | | | | | |
| 13 | low-bed with Trailer ≥50 ton | ≥2010 GC | 1 | | | | | | |
| 14 | high bed with Trailer ≥35 ton | ≥2010 GC | 2 | | | | | | |
| 15 | jet truck (j-truck) ≥6000Lit | ≥2010 GC | 5 | | | | | | |
| 16 | Asphalt Distributer (≥6000 liter Tanker Capacity, ≥2m Spraying Width, Engine Capacity ≥150 hp | ≥2005 GC | 2 | | | | | | |

ስለዚህ ፤

1. ተጫራቾች አግባብነት ያለው ለዘመኑ የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ፣ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፍኬት፣ አግባብነት ያለው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከአዲስ አበባ ከተማ ኮንስትራክሽን ቢሮ የግብር ከፋይ ሰርተፍኬት እና በጨረታ መወዳደር የሚያስችል የዘመኑን ግብር የከፈሉበትን ታክስ ክሊራንስ ሰርተፍኬት እንዲሁም በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ድረ ገፅ (WWW.PPA.gov.et) የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ መመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ተጫራቾች በሰዓት ለኪራይ አገልግሎት ለሚወዳደሩባቸው የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊብሬ ወይም በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ /ውልና ማስረጃ/ የተረጋገጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊብሬ ውክልና ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ በጨረታ ሰነዱ ክፍል 6 /ስድስት/ አባሪ ሁለት በቀረበው ቅፅ መሰረት በማረጋገጥ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡
2. ተጫራቾች የጨረታውን ሠነድ የማይመለስ ብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል ይህ ማስታወቂያ መጀመሪያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከባለሥልጣኑ መ/ቤት የፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 135 መውሰድ ይችላሉ፡፡
3. ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ዋስትናው ከታወቀ ባንክ በባንክ ጋራንቲ ወይም በ Certified Payment Order (CPO) ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ በተጫራቾች የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ተጫራቾች ባቀረቡት የማሽነሪ ብዛት መጠን የሚወሰን ሲሆን፣ ባለስልጣን መ/ቤቱ የተፈለገውን የማሽነሪ ብዛት በሙሉ የሚያቀረቡት የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ከላይ በሰንጠረዥ በተገለፀ መሰረት ይሆናል፡፡ ከባንክ የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (Bid Bond) ለ120 ቀናት ፀንቶ የሚቆይ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. ማንኛውም ተጫራች የመጫረቻ ሰነዱን በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ከላይ በሰንጠረዥ የጨረታ መዝጊያ ተብሎ እስከ ተጠቀሰው ቀንና ሰዓት በባለሥልጣኑ መ/ቤት 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 109 በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በሚገኙበት ከላይ በሰንጠረዥ የጨረታ መክፈቻ ተብሎ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት በባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት ይከፈታል፡፡

መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡

**አድራሻ፡-(ሳርቤት ፑሽኪን አደባባይ አጠገብ)**

**ስልክ ቁጥር 011-3-71-41-03 /011-3-72-28-15**

**የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን**

## ከአዲስ አበባ ከተማ ኤሌክትሪክ አገልግሎት
### ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# ኤኤምአይ (AMI) ስማርት ቆጣሪ ለደንበኞች ያለው ፋይዳ ብዙ ጠቀሜታ

የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት አቅርቦት ሴክተር ባሕሪ በአይነትም ሆነ በመጠን እያደገ የሚሄደውን የደንበኛ ፍላጎት ለማርካት ወቅታዊ የቴክኖሎጂ ውጤትን በግብዓትነት መጠቀም ይጠይቃል። የአገልግሎት አቅርቦቱ ሥራውን በተሻለ ለማከናወን የሚያስችሉ፣ ጊዜና ወጪን የሚቀንሱና የደንበኞች እርካታን የሚያሳድጉ ዘመኑ ያፈራቸውን የቴክኖሎጂ መገልገያዎችና የአሠራር ዘዴዎችን መጠቀም የደንበኞችን ፍላጎት በተሻለ ከማርካትም ባለፈ የተቋሙን ራዕይና ተልዕኮ ለማሳካት ጠቀሜታው የጎላ ነው።

ይህን እውነት ከግምት ውስጥ በማስገባት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኤሌክትሪክ አገልግሎት ቢሮ በዘርፉ አገልግሎት ላይ የዋሉ ወቅታዊ የቴክኖሎጂ ውጤቶችንና የአሠራር ሥርዓቶችን አጥንቶ ሥራ ላይ እያዋለ ይገኛል። ከነዚህም መካከል የኤሌክትሪክ ኃይል ብክነትን ለመቀነስ፣ በቢል ሽያጭ እና ገንዘብ አሰባሰብ ላይ እየታዩ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ እንዲሁም የደንበኞችን እርካታ ለማሳደግ ከፍተኛ ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ደንበኞች ቀደም ሲል ለረጅም ጊዜ ሲገለገሉበት የነበረ አክቲቭ ሪአክቲቭ ኤሌክትሮ ሜካኒካል ቆጣሪዎችን እጅግ ዘመናዊ በሆኑ "AMI DLMS (Advanced Metering Infrastructure)" ስማርት ኤሌክትሪክ ቆጣሪዎች በመቀየር ላይ ይገኛል። ከዚህ አኳያ እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎችን አስመልክቶ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኤሌክትሪክ አገልግሎት አውቶሜሽን እና ኢነርጂ ማኔጅመንት ክፍል ኃላፊ አቶ ዘሪሁን አበበ የሰጡንን ማብራሪያ እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ በፓይለት ሙከራ አምስት ሺ "AMI DLMS" ቆጣሪዎች እንዲቀየሩ እቅድ ተይዞ የነበረ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ አንድ ሺ 865 ቆጣሪዎች ለአዲስ አበባ ሪጂን ተመድቦ ሥራዎች በመሠራት ላይ ናቸው። ለአዲስ አበባ ሪጂን ከተመደቡት ቆጣሪዎች ውስጥ አንድ ሺ 500 የተቀየሩ ሲሆን ከኤኤምአይ (AMI) ሲስተም እና ኤስኤፒ (SAP) ጋር ውህደት (integration) ተሰረቶ ቢል እየወጣላቸው የሚገኙ ደንበኞች አንድ ሺ 100 ደርሳል፡፡

በ2015 በጀት ዓመት ከስምንት ሺ በላይ ደንበኞችን በኤኤምአይ (AMI) ቆጣሪ ለማስተናገድ ዕቅድ ተይዞ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በመሰብሰብ ላይ ይገኛል። ስለዚህ የቀሩትን ለረጅም ጊዜ የሠሩ አክቲቭ ሪአክቲቭ ኤሌክትሮ ሜካኒካል ቆጣሪዎችን ለመቀየርና አዳዲስ የከፍተኛ ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ደንበኞችን በኤኤምአይ ቆጣሪ በማስተናገድ የተቋሙን ገቢ ለማሳደግና የደንበኞችን ፈላጎት ለማርካት በትኩረት በመሠራት ላይ ነው። በመሆኑም የቆጣሪ መቀየርና የመረጃ መሰብሰብ ሥራው ላይ ላሉ የተቋሙ ሠራተኞች ደንበኞች አስፈላገውን ትብብር ሊያደርጉ ይገባል።

ኤኤምአይ (AMI DLMS or Advanced Metering Infrastructure) ቆጣሪ ለደንበኞች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አለው። ለአብነተም ደንበኞች በቀላሉ አፕልኬሽኑን ሞባይላቸው ላይ በመጫን ያላቸውን ወርሃዊ ፍጆታ በቀላሉ ማወቅ ያስችላል። መብራት በሚጠፋበት ጊዜ ስማርት ቆጣሪው መረጃ ወደ መቆጣጠሪያ ማዕከል ስለሚልክ ደንበኞች ስልክ ደውለው መብራት እንደጠፋባቸው ማሳወቅ ሳይኖርባቸው ባለሙያው በቀጥታ እንዲያውቅ ያስችላል። ቆጣሪው ከሰው ንክኪ የፀዳ በመሆኑ ደንበኞች በቆጣሪ ንባብ አስመልክተው የሚያነሱትን ቅሬታ ሙሉ በሙሉ ያስቀራል።

ከዚህ ባሻገር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር ኤሌክትሪክ አገልግሎት ቢሮ ከአራቱ ዲስትሪክቶች ጋር በመሆን የኤሌክትሪክ ኃይል ብክነትን ለመከላከል እና የተቋሙን ገቢ ለማሳደግ የነጠላ ፌዝና የፓወር ቆጣሪዎችን ይመረምራል። እንዲሁም የድርጅቱን ገቢ ከማሳደግና በሀገር አቀፍ የሚባክነውን ኢነርጂ ለተገቢው ልማት እንዲውል የሚደረገውን ጥረት ለማገዝና ከድርጅቱ ደንብና አሠራር ውጪ የሆኑ ተግባራትን ወይም አሠራሮችን ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የማድረግ ሥራ የቢሮው አበይት ተግባር ነው፡፡

በሌላ በኩል የኤሌክትሪክ ኃይል ስርቆት ከሥራው ውስብስብነት አንፃር ግኝቱ አነስተኛ ቢሆንም የቁጥጥር ሥራው ታቅዶና ድንገተኛ ፍተሻ በማድረግ የሚከወን ነው፡ ፡ በምርመራ ወቅት የሚገኙ በተለይም የከፍተኛ ኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚዎች ለረዥም ጊዜ የፍጆታ ቢል እንዲሁም ማባዣ ስህተት ያለባቸውን በማረም ቢል እዲዘጋጅላቸው ይደረጋል፡፡ በዋናነት ለኤሌክትሪክ ኃይል ብክነቱ አስተዋፅኦ አላቸው ተብሎ ከሚሠሩ ሥራዎች ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በትክክል የማይሠሩ፣ የተቃጠሉና የቆሙ ቆጣሪዎች በወቅቱ እንዲቀየሩ ማድረግ እና ውዝፍ የፍጆታ ክፍያ እንዲከፍሉ ወደ ሲስተም መጫን፤ በምርመራ ወቅት የታሪፍ ለውጥ የሚያስፈልጋቸውን ደንበኞች በወቅቱ እንዲቀየር ማድረግ፤ በምርመራ ወቅት ቢል የማይወጣላቸው ደንበኞችን ወደ ሲስተም እንዲገቡ ማድረግ፤ በምርመራ ወቅት ያልተፈቀደ የኃይል ጭነት የሚጠቀሙትን መቆጣጠር፤ ከቆጣሪው ልኬት ውጪ የተገጠመ አውቶማቲክ ፊዩዝን መቀየር እና የኃይል ስርቆትን መቆጣጠር ናቸው። እንዲሁም ከዝቅተኛና ከፍተኛ ኢንድስትሪ ደንበኞች የተገኘ የማባዣ ስህተት ከመለየት አኳያ በርከት ያሉ ስራዎች ተሠርተዋል። እንደማሳያ በ2014 በጀት ዓመት ከላይ በተዘረዘሩት ሥራዎች በብር ሲሰላ 319 ሚሊዮን 890 ሺ 216 ነጥብ 66 ብር ገቢ ተገኝቷል፡፡

በጥቅሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር ኤሌክትሪክ አገልግሎት አውቶሜሽን እና ኢነርጂ ማኔጀመንት ክፍል ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የአዲስ አበባ አስቸኳይ ጥገና ክፍልን በሬዲዮ ኮሙዩኒኬሽን በማስተሳሰር የጥገና ሥራውን የተቀላጠፈ በማድረግ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። የመካከለኛ ቮልቴጅና ዝቅተኛ ቮልቴጅ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ሲቋረጥ በሬዲዮ ኮሙዩኒኬሽን አማካኞነት የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ስለሥራው ክትትል እንዲያደርጉ አስችሏል። በተጨማሪም የሬዲዮ ኮሙዩኒኬሽን የማይደርስባቸው ቦታዎችን በማጥናት ከዋናው መስሪያቤት ጋር በመሆን የማስፋፋት ሥራ ለመሥራት በዝግጅት ላይ እንደሆነ የክፍል ኃላፊው አቶ ዘሪሁን አበበ ገልፀዋል፡፡

## አድራሻ

ኢ.ሜል / E-Mail= aacaeucommunication30csc@gmail.com
ፌስቡክ/ Facebook= https://www.facebook.com/AAREUofficial
ቲዊተር/ Twitter = https://twitter.com/AARE_Utility
ቴሌግራም/ Telegram = https://t.me/addisababaelectricutility
ስልክ/ TELE = 011-636-60-00
= 0116367133

የአዲስ አበባ ከተማ ኤሌክትሪክ አገልግሎት

ahadubank.com

## ለተከበራችሁ የአሐዱ ባንክ ባለአክሲዮኖች

ጥቅምት 12 ቀን 2015 ዓም በተካሄደው የባንካችን 1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ፤ በምስረታ ወቅት ተፈርመው ክፍያቸው ያልተጠናቀቁ አክሲዮኖችን በተመለከተ፤ እስከ ህዳር 15 ቀን 2015 ዓም ድረስ ሙሉ በሙሉ ተከፍለው እንዲጠናቀቁ ውሳኔ መተላለፉ ይታወሳል።

በመሆኑም፤ ቀሪ ድርሻችሁን ያልከፈላችሁ ነባር ባለአክሲዮኖች ለመጨረሻ ጊዜ እስከ ህዳር 15 ቀን 2015 ዓም ድረስ ቀሪ ክፍያችሁን ከፍላችሁ እንድታጠናቅቁ የዳይሬክተሮች ቦርድ ያሳስባል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ያልተከፈሉ አክሲዮኖችን በተመለከተ፤ የዳይሬክተሮች ቦርድ በጉባዔው በተሰጠው ሙሉ ኃላፊነት መሰረት በሚያወጣው መርሐ ግብር ለነባርም ሆነ ለአዳዲስ ባለአክሲዮኖች አክሲዮኖቹ እንዲተላለፉ እንደሚደረግ ለማስታወስ እንወዳለን።

የዳይሬክተሮች ቦርድ ጽ/ቤት
አሐዱ ባንክ
ከብዙዎች ለብዙዎች!!!

Ahadu Bank